# የአርጐባ ብሔረሰብ የወሊድ ስነ ስርዓት ክዋኔ ትንተና

# An Analysis of the Birth Rite of the Argobba Ethnic Group

**እታገኘሁ አስረስ[1]፣ ዘሪሁን አስፋው[2]፣ የኔዓለም አረዶ[3] እና መሐመድ አሊ[4]**

**Etagegnehu Asres, Zerihun Asfaw, Yeniealem Aredo, and Mohammad Ali**

## አጠቃሎ

ይህ ጥናት የአርጐባ ብሔረሰብን የወሊድ ስነ ስርዓት ክዋኔ የመተንተን ዋና ዓላማ ያለው ነው፡፡ የጥናቱን ዓላማ ለማሳካት ካልዓይና ቀዳማይ መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡ ካልዓይ መረጃ ቀደም ብለው የተሰሩ የጽሁፍ ምንጮችን በማንበብ የተገኘ ሲሆን ቀዳማይ መረጃ ለማግኘት የመስክ ስራ ተከናውኗል፡፡ በመስክ መረጃ የተሰበሰበባቸው ዘዴዎች ምልከታ፣ ቃለመጠይቅና ቡድን ተኮር ውይይት ሲሆኑ መረጃ ሰጪዎች በዓላማ ተኮርና ጠቋሚ የንሞና ዘዴዎች ተመርጠዋል፡፡ የተሰበሰበው መረጃ ከዓይነታዊ የመረጃ መተንተኛ ዘዴ ውስጥ የኢትኖግራፊ ጥናት ሞዴልን በመጠቀም ተተንትኗል፡፡ የጥናቱ ግኝት እንደሚያሳየው የአርጐባ ብሔረሰብ የወሊድ ስነ ስርዓት ክዋኔ በሶስት ደረጃዎች ሊከፈል የሚችል ነው፡፡ በክዋኔው ስነቃል (ዱዓዎች፣ ዝኪሮች፣ መማፀኛዎች፣ መልካም ምኞትን መግለጫዎች፣ ምሳሌያዊ አነጋገሮች፣ ዝየራዎች)፣ ቁሳዊ ባህል (ባህላዊ ምግብና መጠጥ፣ አልባሳት፣ የማዋለጃ ቁሳቁሶች፣ የእንግዴ ልጅ መቅበሪያ ቁስ)፣ ማህበራዊ ልማድ (እምነቶች፣ ባህላዊ ሕክምና፣ ስም አወጣጥ፣ የፀጉር አሰራር፣ ጭስ መሞቅ) ፎክሎሮች ተለይተዋል፡፡ ቃላዊ (የዱዓ ቃላት)፣ ቁሳዊና (ገንፎ) ድርጊታዊ (ጣትን በገበታ ዙሪያ ማድረግ፣ ገበታን ከፍ ማድረግ፣ ድፍን ቅል አጥቦና አልጋ ላይ ማድረግ፣ የወላድ ቡና መጨበጥና ቡናን ምጣድ ላይ አድርጐ መጠበቅ) ትዕምርቶች ተለይተው ፍቺዎቻቸው ቀርበዋል፡፡ ስነ ስርዓቱ ማህበራዊ፣ ስነ ልቡናዊና፣ እሴቶችን የመትከል ፋይዳዎች አሉት፡፡ ዘመናዊ የህክምና ተቋማት ማዋለጃዎቻቸውን በባህሉ መሰረት ማስተካከል ቢችሉ፣ የነፍሰጡር የምግብ ክልክሎች ነፍሰጡር ልታገኝ የሚገባውን ንጥረ ነገር የሚያሳጣ መሆን አለመሆኑና አንዳንድ የወሊድ ክዋኔዎች (ለምሳሌ፣ መነቅነቅ፣ ሆድ ማሸት) ከጤና አንፃር የሚያስከትሏቸው የጤና ጉዳቶች ካሉ በወረዳው የጤና ጽ/ቤት ጥናት ተከናውኖ ጉዳቱ ቢለይ ጥሩ ነው፡፡

**ቁልፍ ቃላት**:- አርጐባ፣ ወሊድ፣ ስነ ስርዓት፣ ክዋኔ

[1] በፎክሎር የፒ. ኤች. ዲ ተማሪ፣ ከፍተኛ የኢንታንጆብል ቅርስ ተመራማሪ፣etag907184@yahoo.com

[2] ተባባሪ ፕሮፌሰር፣ አማርኛ ቋንቋ፣ ሥነጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ጥናቱን ሲያማክሩ የነበሩ እና አሁን በህይወት የሌሉ፡፡

[3] (ዶ/ር)፣ በቁሳዊ ባህል ረዳት ፕሮፌሰር፣ አማርኛ ቋንቋ፣ ሥነጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል፣ አአዩ፡፡

[4] (ዶር)፣ በሀገረሰባዊ ባህል ረዳት ፕሮፌሰር፣ አማርኛ ቋንቋ፣ ሥነጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል፣አአዩ፡፡

**Abstract**

This study has the main objective of analyzing the performance of the birth rite of the Argobba ethnic group. Secondary and primary data were collected to achieve the objective of the study. Secondary data was obtained by reading earlier written sources, and fieldwork was conducted to obtain primary data. The methods of field data collection are observation, interview, and focus group discussion, and informants were selected by purposive and snowball sampling methods. The collected data were analyzed using an ethnographic research model from a qualitative data analysis method. According to the findings of the study, the performance of the Argobba birth rite can be divided into three stages. In the performance, oral traditions (prayers, Zəkiroč, supplications, expressions of good wishes), material culture (traditional food and drink, clothing, birthing materials, placenta burial material), and social custom (beliefs, Ziyarawoč, traditional medicine, naming, hairstyles, getting smocked Azəgaro and Wäyəba smokes) folklores have been found. Verbal (words of prayer), material (porridge), and action (putting fingers around a plate, raising a plate, washing a calabash and putting it on a bed, holding coffee and keeping it on a pan) symbols and their interpretations are presented. The rite has social, psychological, and justification benefits. It would be good if modern medical institutions could adjust their delivery rooms according to the tradition if the district health office conducts a study to determine whether or not pregnant food habits are depriving the pregnant of the nutrients they should be getting and if there are any health risks caused by certain performances (e.g., shaking, belly rubs) in terms of health.

**Keywords**: Argobba, Birth, Ritual, Performance, Rite

## 1. መግቢያ

ይህ ጥናት የስነ ስርዓት አንድ ፈርጅ በሆነው የህይወት ሽግግር ስነ ስርዓት ላይ ትኩረት ያደረገ ሲሆን የጥናቱ ዋና ማተኮሪያ የሆነው የህይወት ሽግግር ስነ ስርዓት ደግሞ የወሊድ ስነ ስርዓት ነው፡፡ ወሊድ የሰው ልጆች ዘር ማስቀጠያ የሆነ መሰረታዊ የህይወት ሽግግር ነው፡፡ ከእርግዝና፣ ከወሊድና ከእናትነት ጋር ተያይዘው የሚከወኑ ስነ ስርዓቶችም የእናቲቱና የጨቅላውም ማህበራዊ ግንኙነት ምልክቶች ናቸው፡፡ ለተወለደው ህፃን የማህበረሰቡ አባልነትን ማግኘቱን የሚያረጋግጡ ሲሆን ለእናቲቱ ደግሞ የእናትነት ሚናም የተጨመረላት መሆኑን የሚያሳዩ ናቸው (Pentikäinen[5] 2011, 788)፡፡ በተለያዩ ባህሎች ውስጥ ወሊድን በተመለከተ

[5] ስራቸውን በእንግሊዝኛ ያቀረቡ ፀሐፍት ስማቸው በእንግሊዝኛ ፊደል የተጠቀሰ ሲሆን በአማርኛ ቋንቋ የጻፉ ደግሞ ስማቸው በአማርኛ ፊደል ተጠቅሷል፡፡

የሚከናወኑ ስነ ስርዓቶች ያሉ ሲሆን ስነ ስርዓቶቹ በነፍሰጡርነት ጊዜ የሚጀምሩና ከወሊድ በኋላም የሚቀጥሉ ናቸው (Bell 1997, 95)።

የአርጐባ ብሔረሰብ በኢትዮጲያ በአራት ክልሎች ማለትም በሐረሪ፣ በኦሮሚያ፣ በአማራና በአፋር ክልሎች ውስጥ ይኖራል (Waldron 1984, 49-50; Trimingham 1965, 223; Abebe 1992, 46, 49)። የብሔረሰቡን መነሻ በተመለከተ ቁርጥ ያለ መልስ የሚሰጥ ትንታኔ የለም። ነገር ግን መልስ የቀረበባቸው ሁለት ዋና ዋና መላምቶች አሉ። የመጀመሪያው መላምት የአርጐባ ብሔረሰብ መነሻ የአረብ ሀገር ነው የሚል ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ የአርጐባ ብሔረሰብ የሀገሪቱ ነባር ሕዝብ ነው የሚል ነው (Abebe 1992, 80)። አህመድ (1999, 18) እንደሚለው የአርጐባ ብሔረሰብ ከዘጠነኛው ምዕተ ዓመት ማብቂያ ጀምሮ እስከ አስራ ስድስተኛው ምዕተ ዓመት ሁለተኛ አጋማሽ ድረስ የራሱ የግዛት ክልልና የአስተዳደር ስርዓት ነበረው። የአስተዳደር ስርዓቱ ሁለት ሲሆኑ የማክዙማይትና የሀሺማይት ወላስማ ሱልጧኔቶች ወይም ስርወ መንግስታት ይባላሉ። በአርጐባ ብሔረሰብ ዘንድ የዘር ሀረግ ማንነትንና የብሔረሰቡን ባህላዊ አንድነት ለመግለጽ የሚያስችል መዋቅር የሚሰጥ ሲሆን በባህል ስርዓቱ ውስጥ ትልቅ ቦታ አለው። ብሔረሰቡ አባዊ በመሆኑ የዝምድናን ሀረግ የሚቆጥረው የወንድ ተወላጆችን መስመር ተከትሎ ነው (Abebe 1992, 253-254)። የአርጐባ ብሔረሰብ አባላት አብዛኛውን ጊዜ የደም ዝምድናን መሰረት በማድረግ በአንድ መንደር ተሰባስበው ይኖራሉ። በአንድ ቤተሰብ ውስጥ ወንድ ልጅ እድሜው ለጋብቻ ደርሶ ሲያገባ ሙሽራዋን ወደ ቤተሰቦቹ ቤት በማምጣት በአንድ ላይ ኑሮን ይጀምራሉ። በመሆኑም በአርጐባዎች መንደር በአንድ አጥር ግቢ ውስጥ የሚገኙ ቤቶች የወንድማማቾች ቤተሰቦችን መኖሪያ ወይም የአባወራውን እና ያገቡ ልጆቹን ቤተሰቦች መኖሪያ የሚይዙ ናቸው ማለት ነው። አንዲት ሴት ስታገባ ኑሮዋን የምታደርገው ከባሏ ወላጆች፣ ወንድሞችና ካልተዳሩ እህቶቹ እንዲሁም ከሌሎች ተድረው ከመጡ ሴቶች ጋር ይሆናል ማለት ነው (Abebe 1992, 257)። ይህ ጥናት በአፋር ክልል፣ አርጐባ ልዩ ወረዳ በሚኖረው የአርጐባ ብሔረሰብ ላይ የተወሰነ ሲሆን በብሔረሰቡ የወሊድ ስነ ስርዓት ክዋኔ ላይ ያተኮረ ነው።

የአርጐባ ብሔረሰብ የመኖሪያ መልክዓ ምድሩን ዙሪያ በሚያዋስኑ ቦታዎች ከሚኖሩ ሌሎች ብሔሰቦች ጋር በጉርብትና አብሮ የሚኖርና የህዝብ ብዛቱም ከጐረቤት ብሔረሰቦች አንፃር ሲታይ አነስተኛ በመሆኑ በቋንቋውና በባህሉ ላይ ጫና የደረሰ ቢሆንም (Abebe 1992, 32, 46-57; Trimingham 1965, 152) ባህሉ በመጥፋት ደረጃ ላይ ግን አይደለም። በጥናት አካባቢው በመገኘትና ምልከታ በማድረግ ከተገኘ መረጃ በተለየ የብሔረሰቡ ባህል በመጥፋት ላይ ያለ ተደርጐ ሲቀርብ (ለምሳሌ፣ Aklilu 2000, 173) መታየቱና ይህንንም ለማሳየት ያለ ተነሳሽነት ብሔረሰቡንና ርዕሰ ጉዳዩን ለጥናት እንዲመረጥ አድርጓል። በተደረገ ፊርጀ ብዙ ዳሰሳ በአርጐባ

ብሔረሰብ የህይወት ሽግግር ስነ ስርዓቶች ላይ የተከናወነ ጥናት አለመገኘቱም[6] ሌላው የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ነው፡፡

የጥናቱ ዋና ዓላማ የብሔረሰቡን የወሊድ ስነ ስርዓት ከክዋኔ፣ ከመዋቅር፣ ከትዕምርትና ከፋይዳ አንፃር መተንተን ሲሆን የአርጐባ ብሔረሰብ በወሊድ ጊዜ የሚከውናቸው ስነ ስርዓቶች ምን ምን ናቸው; የክዋኔው መዋቅር ምን መልክ አለው; በክዋኔው ውስጥ ያሉ ሌሎች የፎክሎር ዓይነቶች ምን ምን ናቸው; በስነ ስርዓቱ ውስጥ ያሉ ትዕምርቶች ምን ምን ናቸው; ስነ ስርዓቱ ለከዋኞቹ የሚሰጠው ግለሰባዊና ማህበራዊ ጠቀሜታ ምንድን ነው; የሚሉ ጥያቄዎች በጥናቱ መልስ አግኝተዋል፡፡

## 2. የጽንሰ ሀሳብ ዳራ

የፎክሎር አንድ ክፍል የሆነው ሀገረሰባዊ ልማድ ከሚይዛቸው የፎክሎር ጉዳዮች መካከል አንዱ ስነ ስርዓት (Ritual) ነው፡፡ የስነ ስርዓትን ምንነት በተመለከተ ተመራማሪዎች ብያኔዎችን ሰጥተዋል፡፡ አብዛኛዎቹ ብያኔዎች ስነ ስርዓቶች በአብዛኛው ትዕምርቶችን የሚይዙ፣ እንቅስቃሴዎችና ድግግሞሾችን የሚይዙ፣ ጅማሯቸውንና ፍፃሜያቸውን የሚያሳዩ ቅንብሮች ያሏቸው፣ የተለየ የመከወኛ ቦታና ጊዜ ያሏቸው፣ ወጥ በሆኑ ድርጊቶች የተገነቡ፣ ቀዳሚ ዓላማቸው ማሻገር የሆነ፣ ድራማዊ መዋቅር ያላቸው፣ ከቴክኖሎጂ የተለዩ፣ ማህበረ - ሀይማኖታዊ ባህርይ ያላቸው፣ በህግ የሚመሩ፣ በጋራ የሚከወኑ፣ ከቀደመው፣ ከአሁኑና ከወደፊቱ ጊዜ ጋር የሚያገናኙና በባህሎች ሁሉ የሚተገበሩ ክዋኔዎች ናቸው የሚሉ ዋና ዋና ሀሳቦችን የያዙ ናቸው (Davis-Floyd qtd. in Grimes 2000, 24; Turner 1982, 79, 81)፡፡ Bell (1997, 102-129) ስነ ስርዓቶችን በስድስት ዋና ዋና ክፍሎች የከፈሉ ሲሆን ከስድስቱ አንዱ የህይወት ሽግግር ስነ ስርዓቶች ናቸው፡፡

የህይወት ሽግግር ጽንሰ ሀሳብ ለመጀመሪያ ጊዜ ትኩረት የተሰጠው በፈረንሳዊው የስነ ሰብዕ ተመራማሪ Gennep ሲሆን ከዚያ በኋላ በእንግሊዝ የስነ ሰብዓ ምሁራን ስራ ውስጥ ዋና ጉዳይ ለመሆን በቅቷል፡፡ የህይወት ሽግግር ስነ ስርዓቶች ከእርግዝናና ወሊድ ጀምሮ እስከ ሞት ድረስ ያሉ ዋና ዋና የሰው ልጅ ህይወት ሽግግሮችን ማለትም ወሊድን፣ ስም ማውጣትን፣ ግርዛትን፣ ትምህርት ማጠናቀቅን፣ ጋብቻን፣ ወዘተ ተከትለው የሚመጡ ስነ ስርዓቶች ናቸው (Gennep 1960, 3; Barnard and Spencer 1996, 737; Feinberg 2004, 311)፡፡

---

[6] የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት ተደርጐ በአርጐባ ብሔረሰብ ላይ ከዚህ ጥናት ርዕሰ ጉዳይ በተለየ የተከናወኑ ጥናቶች (ነጋሽ 1981፣ ተስፋዬ 2000፣ አዲሱ 2000፣ ዐቢዩ 2005፣ እታገኘሁ 2010፣ ሰይድ 2015) እና በዚህ ጥናት ርዕሰ ጉዳይ ነገር ግን በሌላ የጥናት አካባቢ የተከናወኑ ጥናቶች (ስራዬ 2005፣ ለማ 2006፣ ድርብወርቅ 2007፣ አፀደ 2007፣ ደስታ 2007፣ አበባ፣ ደስታ፣ ፍሬህይወት 2015) ተገኝተዋል፡፡ ነገር ግን በአርጐባ ብሔረሰብ የህይወት ሽግግር ስነ ስርዓቶች ላይ የተከናወነ ጥናት አልተገኘም፡፡

Mazama (2009, 571) እንደሚሉት የህይወት ሽግግር ስነ ስርዓቶችን የመከወኛ ጊዜ የሚወስነው በአብዛኛው ማህበራዊ ህግ እንጂ የስነ ህይወት ቅደም ተከተል አይደለም፡፡ በአካል መወለድ፣ ፊት ላይ ፂም መብቀል፣ የሆርሞን ለውጥ እና በማህበረሰቡ በአግባቡ መታወቅና የአንድ ማህበራዊ ቡድን አባል ለመሆን ተቀባይነትን ማግኘት ሁለት ጉዳዮች ናቸው፡፡ የህይወት ሽግግር ስነ ስርዓቶችን የመከወኛ ጊዜያት የሚወስነው ቅቡል የሆነው የማህበረሰብ ባህል ነው፡፡

ወሊድ ከወላጇም ሆነ ከሚወለደው ህፃን አንፃር ትልቅ ቦታ ያለው ሽግግር ነው፡፡ እርግዝናና ወሊድ ከየትኛውም የሰው ልጅ የህይወት ሽግግር የበለጠ የፎክሎር ክዋኔዎች ይከወንባቸዋል፡፡ እነዚህ ክዋኔዎች ከእርግዝናና ወሊድ ጋር የተያያዙ እምነቶች፣ ልማዶችና ተግባራት ሲሆኑ እነዚህም ከወላድነት፣ ከሚወለደው ህፃን ፆታ ምርጫ፣ የምጥ ህመምን ከመቀነስ፣ ከሚወለደው ህፃን የወደፊት እጣ ፈንታ ጋር፣ ወዘተ የተያያዙ ናቸው (Watts 2007, 67; Grimes 2000, 36-37)፡፡

Longhurst (1999, 77-78, 82, 86) እንደሚሉት የእርግዝና ወቅት ትኩረት የሚሰጠው ጊዜ ነው፡፡ ነፍሰጡሯ ከተለያዩ ሰዎች አመጋገብን፣ ወሊድን፣ ጡት ማጥባትን፣ የህፃን እንክብካቤንና አስተዳደግን፣ ወዘተ በተመለከተ በርካታ ምክሮች ይለገሷታል፡፡ ምክሩ በመልካም ጐኑ ሊታይ የሚችልና አጋዥ ቢሆንም በነፍሰጡሯ ላይ ገደብ የሚጥል፣ ነፃነቷን የሚጋፋና እንደ ህመምተኛ የሚያስቆጥራት ነው ባይ ናቸው፡፡

Han (2004, 52) በወሊድ ጊዜ ምጥ፣ የልምድ አዋላጆች ሚና፣ ለእናቲቱና ለህፃኑ የሚደረግ እንክብካቤ፣ የመንፃት ስነ ስርዓት ዋና ዋና ጉዳዮች ናቸው፡፡ የዘመናዊ ህክምና መስፋፋት ለአራሷና ለህፃኑ በቂ የህክምና እንክብካቤን እንዲያገኙ ቢያስችልም ማህበረሰቡ ትኩረቱን እንዲቀንስ በማድረግ ወሊድ የነበረውን የጋራ ማህበረሰባዊ አውድ እንዲያጣ አድርጓል፡፡

### 3. የንድፈ ሀሳብ ማሕቀፍ

የአርጐባ ብሔረሰብን የወሊድ ስነ ስርዓት ለመተንተን የክዋኔ ንድፈ ሀሳብ፣ መዋቅራዊ ንድፈ ሀሳብ፣ ትዕምርታዊ ንድፈ ሀሳብና ተግባራዊ ንድፈ ሀሳብ ጥቅም ላይ ውለዋል፡፡ ክዋኔ ከሌሎች ድርጊቶች የተለዩ ይሆኑ ዘንድ የተቀነበቡ ትርጉም ያላቸውን የድርጊት ቅደም ተከተሎችን ማቅረብ ማለት ሲሆን ክዋኔ የሚከሰተው እንቅስቃሴ ሲደረግና ምን እየተደረገ እንደሆነ ለሌሎች ለማሳየት ጥረት ሲደረግ ነው (Bronner 2007, 90)፡፡ መዋቅራዊ ንድፈ ሀሳብ የነገሮችን መዋቅርና የመዋቅሩ ንዑሳን ክፍሎች እርስ በርስ ባላቸው ግንኙነት ላይ ትኩረት ያደርጋል፡፡ ንዑሳን ክፍሎቹ በተፈጥሮ የመዋቅሩ አካላት የሆኑና ትንተና በሚያደርገው ሰው የሚደረስባቸው ናቸው (Storey 2018፣ 128-129)፡፡ የስነ ስርዓቱን መዋቅር ለመለየት የGennep (1960) ባለ ሶስት ደረጃ ሞዴል (መለየት፣ ሽግግርና መቀላቀል) ጥቅም ላይ ይውላል፡፡ ትዕምርቶች የስነ ስርዓቶች ዋና ጉዳይና ሊቀነሱ የማይችሉ ክፍሎች ናቸው፡፡ የስነ ስርዓት ትዕምርቶች ጥናትም በስነ ስርዓቶች

ውስጥ ምን ዓይነት ትዕምርቶች ጥቅም ላይ እንደዋሉ ከመለየት ባሻገር ትዕምርቶቹ እርስ በርስ ያላቸውን ግንኙነትና የያዙትን ትርጉም መለየት አስፈላጊ ነው (Seligman et al 2008, 4)፡፡ ለተግባራዊ ንድፈ ሀሳብ ትልቁን ሚና የተወጡት እንግሊዛውያኑ Malinowski እና Radcliffe-Brown ናቸው፡፡ Malinowski ከግለሰብና ለመኖር ከሚያስፈልጉት መሰረታዊ ፍላጐቶች የሚነሱ ሲሆን Radcliffe-Brown ከማህበረሰብና ለመኖር አስፈላጊ ከሆኑት ነገሮች ይነሳሉ፡፡ የMalinowski ተግባራዊ ንድፈ ሀሳብ መሰረት ያደረገው የሰው ልጅን ስነ ህይወትና ስነ ልቡና ሲሆን ምግብ፣ ዘር መተካት፣ አካላዊ ምቾት፣ ደህንነት፣ ግንኙነት፣ እንቅስቃሴና እድገት የማግኘት ሰባት የሰው ልጅ መሰረታዊ ፍላጐቶች ድምር ነው፤ በባህል ውስጥ ያለ ማንኛውም ማህበራዊ ተቋምና ልማድ እነዚህን ፍላጐቶች ለማሟላት የቆመ ነው የሚል መሰረት አላቸው፡፡ Radcliffe-Brown መዋቅራዊ ተግባራዊ መንገድን የሚከተሉና (Structural functionalist) በማህበራዊ መዋቅር ላይ ትኩረት የሚያደርጉ ናቸው (Malinowski 155-157, 171; Radcliffe-Brown 1952, 178-184)፡፡

በአርጐባ ብሔረሰብ የወሊድ ስነ ስርዓት ክዋኔ ውስጥ ያሉ አላባውያንን ለመለየት የክዋኔ ንድፈ ሀሳብ፣ የክዋኔውን ንዑሳን ክፍሎች ለመለየት መዋቅራዊ ንድፈ ሀሳብ፣ ለተለየ ትርጉም የቆሙ ቁሶችን፣ እንቅስቃሴዎችን፣ ድርጊቶችን፣ ሀሳቦችን፣ ቃላትንና ግንኙነቶችን ለመረዳት ትዕምርታዊ ንድፈ ሀሳብ እና የስነ ስርዓቱን ፋይዳ ለመለየት ተግባራዊ ንድፈ ሀሳብ ጥቅም ላይ ውለዋል፡፡

## 4. የአጠናን ዘዴ

ይህን ጥናት ለማከናወን ካልዓይና ቀዳማይ መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡ በቤተ መጻሕፍትና ሌሎች ተቋማት የሚገኙ የታተሙና ያልታተሙ የመረጃ ምንጮችን በመመልከት ካልዓይ መረጃ የተሰበሰበ ሲሆን ቀዳማይ መረጃ ለማግኘት የመስክ ስራ ተከናውኗል፡፡ የአርጐባ ብሔረሰብ ከሚኖርባቸው 13 ቀበሌዎች ውስጥ ስድስቱ ማለትም ጋቸኔ፣ ገበሮች፣ ላይ መጠቅለያ፣ ጨኖ፣ አባሊና ጉዜ ቀበሌዎች በናሙናነት ተመርጠው የመረጃ መሰብሰብ ስራው ተከናውኗል፡፡ መረጃ ለመሰብሰብ ጥቅም ላይ የዋሉ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ምልከታ፣ ቃለ መጠይቅና ቡድን ተኮር ውይይት ናቸው፡፡ በቃለ መጠይቅ ዘዴ በዓላማ ተኮርና በጠቋሚ የንሞና ዘዴዎች ለተመረጡ 30 መረጃ ሰጪዎች ከፊል ነፃ እና ነፃ ቃለመጠይቆች ተደርገው መረጃ የተሰበሰበ ሲሆን ቃለመጠይቅ የተደረገላቸው የልጆች እናቶችና አባቶች፣ የልምድ አዋላጆች፣ በጤና ተቋማት የእርግዝና ክትትል እያደረጉ ያሉና ክትትል የሌላቸው ነፍሰጡሮች፣ ለወሊድ ጤና ተቋም የገቡ ሴቶች፣ በጤና ተቋምና በቤት ውስጥ የወለዱ አራሶች፣ አዋላጅ ነርሶች፣ የባህል ህክምና እውቀት ያላቸው ሰዎች፣ የሀይማኖት አባትና ተማሪ ናቸው፡፡ በመስክ የተሰበሰቡ መረጃዎች በመስክ ማስታወሻ፣ በመቅረፀ ድምጽ፣ በፎቶግራፍና በቪዲዮ ካሜራዎች ተቀርፀዋል፡፡ መረጃው ከዓይነታዊ የመረጃ መተንተኛ ዘዴዎች ውስጥ ኢትኖግራፊ የጥናት ሞዴልን በመጠቀም ተተንትኗል፡፡ ጥናቱ ሲከናወን የጥናትና ምርምር ስነ ምግባር ደንቦችንና እያንዳንዳቸው የሚይዟቸውን ዝርዝር ሁኔታዎችን ተግባራዊ ለማድረግ ጥረት ተደርጓል፡፡

## 5. የአርጐባ ብሔረሰብ የወሊድ ስነ ስርዓት ክዋኔ፣ መዋቅርና ትዕምርት

በዚህ ክፍል የብሔረሰቡ የወሊድ ስነ ስርዓት ክዋኔ ከመዋቅር አንፃር የቀረበ ሲሆን ትዕምርታዊ ጉዳዮች ተለይተው ፋካሬያዊ ትርጉማቸው ቀርቧል፡፡

### 5.1. መለየት

በአርጐባዎች የወሊድ ስነ ስርዓት ክዋኔ አንዲት ሴት ነፍሰጡር መሆኗን እርሷና በዙሪያዋ ያሉ ሌሎች ሰዎች ካወቁበት ጊዜ ጀምሮ ያለው የእርግዝና ጊዜዋ ከቤተሰቧ አባላት፣ ከፆታ አቻዎቿና ከማህበረሰቡ የምትለይበት ጊዜ ነው፡፡ ለነፍሰጡር የሚደረግ እንክብካቤ፣ የነፍሰጡር ክልክሎችና የሚሰጥ ምክር፣ የአምሮት ስነ ስርዓት ክዋኔና ለወሊድ የሚደረግ ዝግጅት የመለየት መገለጫዎች ናቸው፡፡

አንዲት ሴት ማርገዟን የምታውቅባቸው ዋና ዋና ምልክቶች የወር አበባ መቅረት፣ የማቅለሽለሽና የድካም ስሜት መኖር እና የምግብ ፍላጐት መቀነስ ናቸው፡፡ በአርጐባዎች ዘንድ እርግዝናን ይፋ ማድረግ ነውር ተደርጐ የሚታሰብ በመሆኑ ማርገዟን ያወቀች ሴት ወዲያውኑ አርግዣለሁ ብላ ለሰው አትነግርም፤ ምስጢር አድርጋ ትቆይና ቤተሰቦቿና ጐረቤቶቿ ነፍሰጡር መሆኗን የሚያውቁት ሁኔታዋን በማየት ነው (ወ/ሮ ሲቲ ፋጡማ መሐመድ፣ 7/2/2013፣ ጋቀ[7]፣ ቃመ[8])[9]፡፡

#### 5.1.1. ለነፍሰጡር የሚደረግ እንክብካቤ

የነፍሰጡሯ ቤተሰብ፣ ሴት ዘመዶቿና ጐረቤቶቿ ያምራታል በማለት እንደ አቅማቸው ለነፍሰጡር የሚሰራ ምግብ ሰርተው ይዘው በመሄድ ነፍሰጡሯን ይጠይቋታል፡፡ ነፍሰጡር ያምራታል ተብሎ ከሚዘጋጁ ምግቦች ውስጥ ጨጓራና ጉበት፣ ጭብጦና አሊጣጠ[10] ዋናዎቹ ናቸው፡፡ የፍየል ወይም የከብት ጨጓራና ጉበት ተከትፎና በበርበሬ ታሽቶ ወይም እንዲሁ በእንጀራ ተሸፍኖ ለነፍሰጡር ይወሰዳል፡፡ ጭብጦው በሰሊጥ የሚጨበጥ ሲሆን አሊጣጦው በዶሮ መረቅ እየተነከረ ከዶሮ ስጋና እንቁላል ጋር ይወሰድላታል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ነፍሰጡር ቤቷ ጥሩ ምግብ ቢኖርም የሰው ቤት ምግብ ይሸታታል፤ ትጓጓለች በሚል ምክንያት የነፍሰጡሯ ጐረቤቶች እንጀራ ቢጋግሩ ትኩሱን አጥፈው፣ በርበሬ ቢያስፈጩና ወጥ ቢሰሩ ቀንሰው ይወስዱላታል (ወ/ሮ አሚና ኢብራሂም፣ 13/2/2013፣ ጋቀ፣ ቃመ)፡፡ የነፍሰጡሯ ጐረቤቶች ነፍሰጡሯን በምግብ ከመንከባከብ በተጨማሪ ነፍሰጡርን ለህመም ይዳርጋሉ ተብለው የሚታሰቡና የጉልበት የሆኑ ስራዎችን በመስራት በጉልበትም ያግዟታል (ወ/ሮ እመይ መሐመድ ነጋሽ፣ 19/2/2013፣ ጋቀ፣ ቃመ)፡፡

---

[7] ጋቸኔ ቀበሌ
[8] ቃለመጠይቅ
[9]ቀዳማይ መረጃ ሲቀርብ  የመረጃ ሰጪው ስም፣ መረጃው የተሰበሰበበት ቀንና ቦታ እና መረጃው የተሰበሰበበት ዘዴ በዚህ መልኩ ተደራጅቶ ቀርቧል፡፡
[10] በስሱ የሚጋገር ቂጣ

ለነፍሰጡር የሚደረግ እንክብካቤ ነፍሰጡሯ ተጋላጭ ነች ተብሎ ከሚታሰቡ በሽታዎች እንድትጠበቅ ማድረግም ነው (ወ/ሮ ከድጀሺ ከማል፣ 19/3/2013፣ ላመቀ[11]፣ ቃመ)፡፡ ልብስ የሰው ዓይን መከላከያ ነው ተብሎ የሚታመን በመሆኑ ነፍሰጡር ሆዷ ገፍቶ እንዳይታይ በተቻለ መጠን መሸፈንና በጣም ሰፊ ልብስ መልበስ እንዳለባት ይታመናል፡፡ ነፍሰጡር ሆዷ ሲገፋ ከቤት ደጅ ስትንቀሳቀስ ለበሽታ የሚዳርግ እርኩስ መንፈስ እንዳያየት ተብሎ ቤቱ አጥር ከሌለው ዙሪያውን አጥር ይታጠራል፤ አጥር ካለውም በክትክታ[12] ሽምጥ እየተጠቀጠቀ ይታደሳል፡፡ በተጨማሪም ነፍሰጡር የሰው ዓይን መከላከያ እንዲሆናት እውቀቱ ባለው ሰው ጽህፈት ተጽፎ በአንገቷ ወይም በክንዷ ላይ ታስራለች (ወ/ሮ አይከዲጅ መሐመድ፣ 29/3/2013፣ ላመቀ፣ ቃመ)፡፡

### 5.1.2. የነፍሰጡር ክልክሎችና ምክር

የመውለጃ ጊዜዋ የቀረበ ነፍሰጡር በምግብና በድርጊት ክልክሎች አሉባት፡፡ ምግብን በተመለከተ ጥራጥሬ፣ አሬራ፣ ማር፣ ሽንኩራ፣ ፓፓዬ፣ ቃሪያና የሎሚ ጭማቂ ምግቧ ውስጥ እንዳይኖር ትከለከላለች፡፡ አሬራ መጠጣት ጽንሱ ጭንቅላት ላይ ቆሻሻ ሆኖ ይጋገራል፣ ማር መብላት ለጽንሱ ትንታ ያመጣበታል፣ ሽንኩራ መብላት ምጥ ያጠናል፣ ፓፓዬ መመገብ ጽንሱን እንዲፋፋ ስለሚያደርግ በወሊድ ጊዜ ምጥ ያጠናባታል፣ ቃሪያ ሲመገቡት እንደሚፋጅ ሁሉ ጽንሱም ላይ መፋጀት ያስከትላል፣ የሎሚ ጭማቂ ምጥ ያለጊዜው እንዲመጣ ያደርጋል (ወ/ሮ ሷቢራ ኡመር፣ 25/4/2013፣ ጨቀ[13]፣ ቃመ) የሚሉ ምክንያቶች የክልከላዎቹ መነሻዎች ናቸው፡፡

ነፍሰጡር በጽንሱ አንገት ላይ እትብት ይጠመጠማል በሚል ምክንያት በመኝታ ጊዜ በጀርባዋ እንዳትተኛና ለመዞር ስትፈልግ ተነስታ መዞር ወደምትፈልግበት አቅጣጫ መዞር እንጂ እንደተኛች እንዳትዞር፣ ጽንሱ ቦታውን እንዲስት ያደርጋል በሚል ምክንያት ስትራመድ ፈጠን ፈጠን እንዳትል፣ በጽንሱ ላይ ጉዳት ያደርሳል በሚል ምክንያት በጣጣቴ[14] እንዳትታከም፣ የሽሉ አቅጣጫ ባልተገባ ሁኔታ እንዲሆንና ወደ ጐን እንዲሰነቀር ያደርጋል ይህ ደግሞ ነፍሰጡሯን አቅም ያሳጣታል ሽንትም ይከለክላታል በሚል ምክንያት እንዳትጠማዘዝና እግሮቿን አጣጥፋ ዝቅ ባለ መቀመጫ ላይ እንዳትቀመጥ፣ ጽንሱ ቦታውን እንዲስት ያደርጋል በሚል ምክንያት ከባድ ስራዎችን እንዳትሰራ፣ ከባድ እቃ እንዳታነሳና እንዳትሸከም እና የወይባ ጭስ ሰውነት ያጠብቃል ተብሎ ስለሚታመን ሰውነቷ ጠብቆ ምጧ እንዳይጠና ወይባ እንዳትሞቅ ትከለከላለች፡፡ ምች ከሚያስመቷት ድርጊቶችም ራሷን መቆጠብ እንዳለባት ይታመናል (ወ/ሮ ሀይሀሊማ ሱለይማን፣ 16/5/2013፣ ገቀ[15]፣ ቃመ)፡፡

---

[11] ላይ መጠቅለያ ቀበሌ
[12] በአካባቢው ተዘውትሮ ለአጥር ስራ የሚውል የዛፍ አይነት ነው፡፡
[13] ጨፍ ቀበሌ
[14] ሽቦ በእሳት እየተጋለ የታመመን አካል በመተኮስ የሚከናወን ባህላዊ ህክምና ነው፡፡
[15] ገበሮች ቀበሌ

### 5.1.3. የአምሮት ስነ ስርዓት

የአምሮት ስነ ስርዓት ነፍሰጡር ሰባት ወይም ስምንት ወር ሲሆናት የሚከወን ስነ ስርዓት ሲሆን የነፍሰጡሯ ቤተሰብ የተለያዩ ምግቦችን አዘጋጅቶ በመሄድ ነፍሰጡሯን የሚጠይቅበት፤ ጐረቤት ተጠርቶ የሚጋበዝበትና ዱዓ የሚደረግበት ስነ ስርዓት ነው። የአምሮት ስነ ስርዓት የሚከወንበት ዋና ዓላማ ነፍሰጡሯ በሰላም እንድትገላገል፣ ምጧ እንዲገራ፣ ጭንቋ እንዲቀል፣ ጤነኛ ልጅ ወልዳ እንድትታቀፍ፣ መጥፎ ነገር ሁሉ ከእርሷ እንዲርቅና በአንፃሩ ጥሩ ነገር እንዲቀርባት ዱዓ እንዲደረግላት ማድረግ ነው (ወ/ሮ ሲቲ ፋጡማ መሐመድ፣ 8/2/2013፣ ጋቀ፣ ቃመ)። ነፍሰጡሯ ከመጥፎ ተከልላ ለጥሩ እንድትቀርብ ማድረጊያ ከሆነ ደግሞ የስነ ስርዓቱ ክዋኔ ነፍሰጡሯን የመጠበቅ ዓላማ ያለው ነው ማለት ነው። በዚህ ምክንያት ስነ ስርዓቱ ነፍሰጡር ከአደጋ የመጠበቅ ስሜት እንዲኖራት የሚያደርግ በመሆኑ ስነ ልቡናዊ ፋይዳ አለው። ነፍሰጡሯ በአምሮት ላይ የሚደረገውም ዱዓ ቀሪ የነፍሰጡርነት እና የወሊድ ጊዜዋን ቀና እንደሚያደርግላት ስለምታምን ሰላምን ያስገኝላታል።

ከዚህ በተጨማሪ ወ/ሮ እመይ መሐመድ ነጋሽ እንደገለፁት ሰዎችን መመገብ ለነፍሰጡሯ በረከት ያስገኛል ተብሎ የሚታመን መሆኑ፣ ስነ ስርዓቱ የነፍሰጡሯ እናት ልጇ ልጅ ልታገኝና ዘር ልትቀጥል በመሆኑ ያገኘችውን ደስታ ማካፈያዋ መሆኑና ስነ ስርዓቱ ለነፍሰጡሯ ብቻ ሳይሆን ለነፍሰጡሯ ቤተሰብ፣ ለሀገር፣ ለታመሙና ለተቸገሩ ሰዎች፣ ወዘተ ዱዓ የሚደረግበት መሆኑ የስነ ስርዓቱ ተጨማሪ የመከወኛ ምክንያቶች ናቸው (19/2/2013፣ ጋቀ፣ ቃመ)።

የአምሮት ስነ ስርዓት ሴቶች የሚያዘጋጁት በመሆኑ በዋናነት የነፍሰጡሯ እናት ኃላፊነት ነው። የነፍሰጡሯ እናት በህይወት ባትኖር እንኳን የቤተሰቡ ኃላፊነት ያለባት ሌላ ሴት፤ በቤተሰብ ውስጥ ሴት ከሌለች ደግሞ አክስት፣ የአጐት ሚስት፣ የወንድም ሚስት፣ ወዘተ ኃላፊነቱን በመውሰድ የአምሮት ስነ ስርዓቱን ዋና በመሆን ታዘጋጃለች (ወ/ሮ ሳሱየ አሊየ፣ 6/7/2013፣ አቀ[16]፣ ቃመ)።

የአምሮት ስነ ስርዓት የሚከወነው ነፍሰጡሯ ሰባት ወይም ስምንት ወር ሲሆናት የነፍሰጡሯ እናት ወይም ስነ ስርዓቱን በሀላፊነት የምታዘጋጀው ሴት በምትመረጠው ቀን ነው። እናት ወይም ሌላዋ ሴት ቀኑን ከወሰነች በኂላ በዚህ ቀን እንመጣለን በማለት ለነፍሰጡሯ ታሳውቃታለች፤ ለእህቶቿ፣ ለወንድሞቿና ለመላው ቤተሰቧ እንዲሁም ለቅርብ ጓደኞቿም በዚህ ቀን ልጄን ለማየት እሄዳለሁ ብላ ታሳውቃለች፤ ተከትለዋት የሚሄዱ ሰዎች የአቅማቸውን ያህል ጭነት እህል ያዘጋጃሉ (ወ/ሮ ሳሱየ አሊየ፣ 6/7/2013፣ አቀ፣ ቃመ)።

የነፍሰጡሯ እናት ወይም ስነ ስርዓቱን የማዘጋጀት ሀላፊነት ያለባት ሌላ ሴት በአምሮቱ ቀን ዋዜማ ነፍሰጡሯ ለአምሮቱ ለምትጠራቸው ጐረቤቶቿ መጥሪያና

---

[16] አባሊ ቀበሌ

ማስተናገጃ ሲሆን በሚችል መጠንና ለስራ እገዛ ከተጠሩ ጐረቤቶች ጋር በመሆን ምግብ ታዘጋጃለች፡፡ ለአምሮት የሚወሰዱ ምግቦች ዳቦ፣ አነባበሮ፣ በዶሮ ወጥ የተነከረ አሊጣጦ፣ የጤፍ እንጀራ፣ ንጥር ቅቤና የተወቀጠ ሰሊጥ ናቸው (ወ/ሮ ሳሱየ አሊየ፣ 6/7/2013፣ አቀ፣ ቃመ)፡፡ ምግቡ ተዘጋጅቶ ካለቀ በኋላ ምግቡን ለመውሰድ የማዘጋጀት ስራ ይሰራል፡፡ አሊጣጦው በተሰራው ዶሮ ተነክሮ ይዘጋጃል፤ አነባበሮው ቅቤና በርበሬ ተመትቶ ይለቀለቅና አይንና አይኑ እየተገጠመ በመሶብ ተደርጐ ይሸፈናል፤ ዳቦውና እንጀራው በመሶብ ተደርጐ ይሸፈናል፡፡ ምግቡ ሁሉ ተዘጋጅቶና ለጉዞ እንዲሆን ተቋጥሮ ካለቀ በኋላ ቡና ይፈላና የቡና ቁርስ ከተጋገረው አነባበሮ ይቀርባል፡፡ በስራው ላይ የተሳተፉ ሁሉ ይሰበሰቡና ዱዓ አድርገው ቡናውን ይጠጣሉ (17/2/2013፣ ጋቀ፣ ም፤ 11/3/2013 እና 25/3/2013 ላመቀ፣ ም)፡፡

በመስክ ምልከታ ወቅት ለነፍሰጡሯ ለወ/ሮ ዘይነባ መሐመድ ጀማል ለሚዘጋጀው የአምሮት ስነ ስርዓት በዋዜማው በነፍሰጡሯ እናት በወ/ሮ ሀሊማ መሐመድ ሰኢድ ቤት ዝግጅቱ ከተጠናቀቀ በኋላ ቡና ተፈልቶ ጀባ[17] ሲባል በስራው ላይ ዋና ተሳታፊ በነበሩት በወ/ሮ በድሪያ መሐመድ አድራጊነትና ስራውን ሲሰሩ በነበሩና በቡናው ስነ ስርዓት ላይ ተሰብስበው በነበሩት ሴቶች ተቀባይነት ወይም አሜን ባይነት ዱዓ የተደረገ ሲሆን (16/2/2013፣ ጋቀ፣ ም) እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

| ዱዓ አድራጊ | ተቀባዮች |
|---|---|
| ፈረጃሽን[18] ቅርብ | አሜን! |
| ደስታሽን ሰፊ | አሜን! |
| አላህ ያርግልሽ | አሜን! |
| አላህ ያክርምሽ | አሜን! |
| ያገሩ ሼህ ከክሽም፣ ከጦስም፣ ተአፋትም[19]፣ ተንቅፋትም ጥብቅ አላህ ያርግልሽ | አሜን! |
| የበረካ[20] ዛፍ አላህ ያርግሽ | አሜን! |
| ሀረግሽም የሚሳብ አላህ ያርገው | አሜን! |
| አበባሽ የማይረግፍ ይሁን | አሜን! |
| ኖረሽ ከርመሽ ደግ ዕድል፣ ደግ ኸቲማ[21] አላህ ይወፍቅሽ[22] | አሜን! |
| አሏሁ መሰሊ ወሰሊም አላ ሰይድና መሐመድ ወአላ አሊ ሰይድና መሐመድ[23] | |

[17] መስጠት፣ ስጦታ
[18] መገላገል፣ እፎይ ማለት
[19] ድንገት የሚመጣ መጥፎ ነገር፣ መዓት፣ አጥፊ ነገር
[20] የተባረከ
[21] መጨረሻ
[22] መግባባት
[23] ዱዓ ተደርጐ ሲያበቃ ዱዓውን የሚመራው ሰው "አሏሁ መሰሊ" የሚል ሲሆን ትርጉሙ "አላህ ምህረትን አውርድ" የሚል ነው፡፡ ተቀባዮች ደግሞ "ወሰሊም አላ ሰይድና መሐመድ ወአላ አሊ ሰይድና መሐመድ" የሚሉ ሲሆን ትርጉሙ "በነቢዩ መሐመድና በቤተሰቦቻቸው ላይ ሰላምታን አውርድ" ማለት ነው (አቶ መሐመድ አቡበከር፣ 6/2/2013፣ ጋቀ፣ ቃመ)፡፡ ይህ የዱዓ መዝጊያ ነው፡፡ ከዱዓ በኋላም ዱዓ አድራጊዎች እርስ በእርስ ይዘያየራሉ ወይም ፊታቸውን አበስ ያደርጋሉ፡፡

ዱዓው የተደረገው ለነፍሰጡሯ እናት ለወ/ሮ ሀሊማ መሐመድ ሲሆን እናቲቱ ደስተኛ ኑሮ እንዲኖራት፣ የአካባቢው ጠባቂ ነው ተብሎ የሚታመንበት በመንፈሳዊነቱ የበቃ ያገሩ ሼህ ከክፉው ሁሉ እንዲጠብቃት በመመኘት ነው። በዱዓው ውስጥ “የበረካ ዛፍ አላህ ያ[ድ]ርግሽ”፣ “ሀረግሽም የሚሳብ አላህ ያ[ድ]ርገው”፣ “አበባሽ የማይረግፍ ይሁን” የሚሉ የዱዓ ክፍሎች ያሉ ሲሆን ዛፍ፣ ሀረግና አበባ ትዕምርታዊ ናቸው። የእነዚህ ትዕምርቶች ፍች የሚገኘው ደግሞ የትዕምርቶቹን ስነ ህይወታዊ ምንነት በመለየት ነው። ዛፍ ቅርንጫፎቹ የሚሰፉና ለሰውም ሆነ ለእንስሳት ከፀሀይና ከዝናብ መጠለያ የሚሆን ነው። አበባ የውበት ጊዜና የፍሬ መሰረት ነው፤ አበባን ቀጥሎ የሚመጣው ፍሬ ነው። ሀረግም ቁመቱ የሚሳብና የሚረዝም ተክል ነው። ዱዓው የተደረገው ዱዓ የተደረገላት ሴት የእጽዋቱን መገለጫ ባህርያት እንድታገኝ፤ እንደ ዛፍ ለሰዎች መጠጊያ እንድትሆን፣ እንደ አበባ ፍሬ የማግኛ ጊዜዋ እንዲረዝም፣ እንደ ሀረግ ዘሯ የሚሳብ እንዲሆን ነው። ምርቃቱ የብሔረሰቡ አባላት ልጅ መውለድንና ዘር መብዛትን በተመለከተ ያላቸውን ከፍ ያለ አመለካከትም ያሳያል።

ነፍሰጡሯ ቤተሰቧ የሚመጣበት ቀን ተቆርጦ እንደተነገራት በእድሜ ከፍ ያሉ ጐረቤቶቿን ቤተሰቤ በዚህ ቀን ስለሚመጣ ተቀበሉልኝ ብላ ትጠራለች፤ ለመቀበያ የሚሆን ምግብና መጠጥ ታዘጋጃለች። አምሮት ወሳጆቹ በአምሮቱ ቀን ዋዜማ ምሽት በነፍሰጡሯ ቤት ሲደርሱ የነፍሰጡሯ ባለቤት ቤተሰብና ነፍሰጡሯ ተቀበሉልኝ ብላ የጠራቻቸው ሰዎች፤ ሴቶቹ ሴቶቹን፣ ወንዶቹ ደግሞ ወንዶቹን ይቀበሏቸዋል (ወ/ሮ ሳሱየ አሊየ፣ 6/7/2013፣ አቀ፣ ቃመ)። በእስልምና ሀይማኖት አስተምህሮ መሰረት በዚህ አይነቱ ስብሰባ ወቅት ወንድና ሴት ተቀላቅሎ ስለማይቀመጥ (Quran, 33:53) ሴቶችና ወንዶች በየተዘጋጀላቸው ስፍራ ለየብቻ ይሆናሉ። የነፍሰጡሯ እንግዶች ከገቡ በኋላ በተዘጋጀው ምግብና መጠጥ ተጋብዘው ወንዶቹ ዱዓ እያደረጉ ያመሻሉ (17/2/2013፣ ጋቀ፣ ም፤ 11/3/2013 እና 25/3/2013 ላመቀ፣ ም)።

ከመስተንግዶው በኋላ የነፍሰጡሯ እናት ወይም አምሮቱን በኃላፊነት ይዛ የመጣችው ሌላ ሴት ለነፍሰጡሯና ለባለቤቷ ለብቻ ተዘጋጅቶ የመጣው አሊጣጦ ሲቀር የመጣውን ምግብ በሙሉ ለሌማት ከፋቾች ካቀረበች በኋላ ሌማት ከፋቾች ዳቦውን፣ አነባበሮውንና እንጀራውን ይቆጥራሉ። ሌማት ከፋቾች ነፍሰጡሯ ቤተሰቧን እንዲቀበሉና ቤተሰቡ ይዞት የሚመጣውን ምግብ በተጠሪው ጐረቤት አባወራ ቁጥር ልክ አድርገው በመሸንሸን እንዲያዘጋጁላት የምትጠራቸው ጐረቤቶቿ የሆኑ አዛውንት ሴቶች ናቸው። ከዚያ በኋላ በማግስቱ ጠዋት ለሚከወነው የገንፎ ስነ ስርዓት የሚጠራውን ጐረቤት ማንነትና ቁጥር በተመለከተ ተነጋግረው ይወስናሉ። በማግስቱ ለሚከወነው የገንፎ ስነ ስርዓት የሚመጣው ጐረቤት የሚጠራው የመጣው ዳቦና አነባበሮ እየታደለው በመሆኑ ዳቦው፣ አነባበሮውና እንጀራው በሚጠራው አባወራ ቁጥር ልክ እንዲደርስ ተደርጎ ይቆረሳል። አዳዮች ምግቡን ተሸክመው በየቤቱ በመሄድ ምግቡን እያደሉና “ነገ ጠዋት እከሌ ቤት ቡና ጠጡ” እያሉ ጥሪ ያስተላልፋሉ (17/2/2013፣ ጋቀ፣ ም፤ 11/3/2013 እና 25/3/2013 ላመቀ፣ ም)።

ለአምሮት ስነ ስርዓት የሚዘጋጀው ብቸኛ ምግብ ገንፎ በመሆኑ በማግስቱ ጠዋት ገንፎ ይገነፋል፤ ማባያም ይዘጋጃል (17/2/2013፣ ጋቀ፣ ም፤ 11/3/2013 እና 25/3/2013 ላመቀ፣ ም)። ገንፎ ከምግብነቱ ባሻገር በዚህ ስነ ስርዓት ላይ መቅረቡ ትዕምርታዊ ያደርገዋል። ትዕምርታዊ ፍችው የሚገኘው ደግሞ የትዕምርቱን ምንነት በመለየት ነው። ገንፎ ለስላሳ፣ ገርና ሲመገቡት ብዙ አላምጡኝ የማይል የምግብ ዓይነት ነው። የአምሮት ስነ ስርዓት የመከወኑ ዋና ምክንያት ደግሞ ነፍሰጡር ስትወልድ ምጧ እንዲገራ፣ በምጥ እንዳትቸገር ዱዓ እንዲደረግላት ማስቻል ነው። በመሆኑም ለስላሳው ገንፎ ገር እንዲሆን ለሚመኙት የነፍሰጡሯ ምጥ ተመሳስሎ የቆመ ይመስላል። ከሌሎች ምግቦች መርጦ ገንፎን የስነ ስርዓቱ ዋና ምግብ ማድረግ የነፍሰጡሯ ምጥ እንደ ገንፎው ገርና ለስላሳ እንዲሆን የመመኘትና የማምሰል ተግባር ነው።

ገንፎው ተገንፍቶ ወንዶች በቅድሚያ ከተስተናገዱ በኋላ የሴቶቹ መስተንግዶ ይቀጥላል። ገንፎው ሲቀርብ የነፍሰጡሯ እናት ቆማ "ቢስሚላሂ ራህማራ ራሂም ለሲቲና ፋጡማ" በማለት ገንፎውን ጀባ ትላለች። ፋጡማ የነብዩ መሐመድ ልጅ ሲሆኑ ወልደው የተባረከላቸው፣ ምጥን የሚያገሩ፣ ምጥን የሚያሳጥሩ፣ ጭንቅን የሚያቀሉ፣ ወላድን የሚቀርቡ፣ ወሊድን የሰላም የሚያደርጉ እንደሆኑ ይታመናል። የአምሮት ስነ ስርዓት ነፍሰጡሯ በሰላም እንድትወልድ በዋናነት ፋጡማ የሚለመኑበት በመሆኑ የነፍሰጡሯ እናት ገንፎው በፋጡማ ስም መዘጋጀቱን በመግለጽ ሰዎችን ለዱዓ ትጋብዛለች ማለት ነው። ከዚያ በኋላ ሴቶቹ በገንፎው ዙሪያ በክብ በመቀመጥ የሁለት እጆቻቸውን ጣቶች በገበታው ክፈፍ ዙሪያ ላይ በማድረግ በእድሜ አንጋፋ የሆኑና ዱዓ ማድረግ የሚችሉ ሴቶች ተመርጠው ዱዓ ያደርጋሉ (17/2/2013፣ ጋቀ፣ ም፤ 11/3/2013 እና 25/3/2013 ላመቀ፣ ም)። ጣቶችን በገበታ ዙሪያ በማድረግ ገበታውን መያዝ ትዕምርታዊ ድርጊት ነው። ገበታው ምጥን እንደሚያገሩ፣ ጭንቅን እንደሚያርቁ በሚታመንባቸው ስም የሚቀርብ በመሆኑ በአፍ ከሚደረገው ዱዓ በተጨማሪ ገበታውን መያዝ አጥብቆ መለመንን፣ መማፀንን የያዘ ትዕምርታዊ ድርጊት ነው።

የነፍሰጡሯ እናት ወይም አምሮቱን በኃላፊነት ያዘጋጀችው ሴት በየመራቂዎቹ ፊት ቆማ ጕንበስ በማለትና እጆቿን በመዘርጋት "አሜን" እያለች ዱዓውን ትቀበላለች (17/2/2013፣ ጋቀ፣ ም፤ 11/3/2013 እና 25/3/2013 ላመቀ፣ ም)። የሚከተለው ዱዓ በምልከታ ወቅት ለወ/ሮ ዘይነባ መሐመድ ጀማል የተደረገ፤ የአምሮት ስነ ስርዓት ላይ ገበታ ቀርቦ ከተደረጉ ዱዓዎች ውስጥ ለማሳያነት የተመረጠ ሲሆን በወ/ሮ አሚና ኢብራሂም መሪነት የተደረገ ነው (17/2/2013፣ ጋቀ፣ ም)።

| ዱዓ አድራጊ | ተቀባዮች |
|---|---|
| በሙሉ አላህ ያውጣት | አሜን! |
| ሙሉ ቀን አላህ ይግጠማት | አሜን! |
| የሰሊጥ ውቂያ አላህ ያድርግላት | አሜን! |
| ሙልጭ ሙልጭልጭ ያድርግላት | አሜን! |

ቀሚሷ አይስማት አሜን!
ባሏም ከጉኗ ተኝቶ አይስማት አሜን!
ጉረቤትም ሳይሰማ አሜን!
የለበሰችው ሽማ ሳይሰማ አሜን!
የአጥር ወፍም ሳይሰማ አሜን!
እንጨቱም ቅጠሉም ሳይሰማ አሜን!
እናትም አባትም ሳይሰማ አሜን!
በሰላም ትገላገል አሜን!
ጭንቅን አያሳየን አሜን!
አማን[24] ትውለድ አሜን!
ልጁም ወንድ ይሁን አሜን!
ምጡም ገር ይሁን አሜን!
አሏሁ መሰሊ ወሰሊም አላ ሰይድና መሐመድ ወአላ አሊ ሰይድና መሐመድ

ዱዓው ነፍሰጡሯ በሰላም እንድትወልድ፣ ምጧ እንዲገራ፣ ያለ ብዙ ጭንቅ እንድትገላገል በመመኘት የተደረገ ነው፡፡ በዱዓው ላይ “በሙሉ አላህ ያውጣት”፣ “ሙሉ ቀን አላህ ይግጠማት”፣ “ልጁም ወንድ ይሁን” እና “የሰሊጥ ውቂያ አላህ ያድርግላት” የሚሉ የዱዓ ክፍሎች ትዕምርታዊ ናቸው፡፡ “በሙሉ አላህ ያውጣት” በተባለው ሙሉነት ከህመም፣ ከመጉደል፣ ይህ ቀረኝ ከማለት ተጠብቆ በሰላም መሻገርን የሚወክል ሲሆን በዚህና በሌሎች ዱዓዎች የሚታየው መውጣት የሚለው ቃል ነፍሰጡሯ ካለችበት የጭንቅ ጊዜ ቀለል ወዳለው ጊዜ ማለፏን፣ መሻገሯን፣ የሚወክል ነው፡፡ “ሙሉ ቀን አላህ ይግጠማት” በተባለው ደግሞ ሙሉ ቀን ችግር፣ ህመም፣ መከራ፣ ስቃይ የሌለበትና በአንፃሩ በገድ የተሞላ ቀንን ይወክላል፤ ነፍሰጡሯ በሚገጥማት ሙሉ ቀን ሙሉ ነገር እንዲገጥማት መመኘት ነው፡፡ “ልጁም ወንድ ይሁን” የሚለው የዱዓው ክፍል በአርጐባዎች ዘንድ ያለን የፆታ ምርጫ ጉዳይ በተመለከተ መረጃ የሚሰጥ ሲሆን በአርጐባዎች ልማድ ከሴት ልጅ ይልቅ የወንድ ልጅ መወለድ እንደሚመረጥ ያሳያል፡፡ “የሰሊጥ ውቂያ” ትዕምርታዊ ፍች የሚገኘው የትዕምርቶቹን ምንነት በመረዳት ነው፡፡ የሰሊጥ ውቂያ እንደሌላው እህል ውቂያ ብዙ ጉልበት አይፈልግም፡፡ አዝመራው ታጭዶና ታስሮ ይከመርና ሲደርቅ እስሩን ወደ ታች መዘቅዘቅና ማራገፍ ብቻ በቂ ነው፤ ምርቱ ይራገፋል፡፡ ምጡን የሰሊጥ ውቂያ ያድርገው ሲባልም ምጡ የሰሊጥ ውቂያን ያህል ይቅለል፣ ብዙ ጭንቅ አይኑረው ማለት ነው፡፡ ቀሚሷ ሳይሰማ፣ የለበሰችው ሽማ ሳይሰማ፣ የአጥር ወፍ ሳይሰማ፣ እንጨቱም ቅጠሉም ሳይሰማ፣ እናትም አባትም ሳይሰማ፣ ወዘተ ትውለድ መባሉም ይህንኑ ሀሳብ የሚያጠብቅና ነፍሰጡሯ ቤተሰብን የሚቀሰቅስ፣ ጉረቤትን የሚጠራ ጭንቅ ሳያገኛት ትውለድ የሚል መልዕክት ያለው ነው፡፡

[24] ሰላም

ዱዓው ካበቃ በኋላ ሁሉም ሴቶች ተዘያይረው ሲያበቁ ከገንፎው ሶስት ጊዜ ተቆንጥሮ በጣባ ይደረግና ነፍሰጡሯ እንድትበላው ይሰጣታል (17/2/2013፣ ጋቀ፣ ም፤ 11/3/2013 እና 25/3/2013 ላመቀ፣ ም)፡፡ ማንም ሰው ከመቅመሱ በፊት ገንፎው ተቆንጥሮ ለነፍሰጡሯ የሚሰጣት ገንፎው ዱዓ የተደረገበት በመሆኑ ቀድማ መቅመሷ የዱዓውን በረከት ያስገኝላታል፤ ዱዓው እንዲደርስላት ያደርጋል ተብሎ የሚታመን በመሆኑ ምክንያት ሲሆን ሶስት ጊዜ መቆንጠሩም አርጐባዎች ነገር በሶስት ይፀናል ብለው ስለሚያምኑና ምርቃቱ እንዲሆንላት በመመኘት ነው፡፡

ገንፎው ተበልቶ ካበቃ በኋላም ሲጀመር በተደረገበት መንገድ ዱዓ ተደርጐ ሴቶቹ ይዘያየሩና ሁሉም ገበታውን ዙሪያውን በመያዝ እልል እያሉ ሁለት ጊዜ ወደላይ ከፍ ምልስ፣ ከፍ ምልስ በማድረግ በሶስተኛው ከፍ አድርገው "ልጁ ተወለደ! ልጁ ተወለደ!" ብለው ገበታው በዚያው ወደ ጓዳ እንዲገባ ይደረጋል (17/2/2013፣ ጋቀ፣ ም፤ 11/3/2013 እና 25/3/2013 ላመቀ፣ ም)፡፡ ከመረጃ ሰጪዎች አንዷ ወ/ሮ አይኔ ይማሙ እንደገለፁት ገበታ ከፍ አድርጐ ወደ ጓዳ ከማስገባት ትዕምርታዊ ክዋኔ ጋር ትይዩ የሆነ ሌላ ክዋኔም አለ፡፡ ይህም ድፍን ቅል ይታጠብና እንደ ልጅ በጨርቅ ተጠቅልሎ "ወለደች! ወለደች!" ተብሎ አጣቢዋ ሴት ቅሉን ወስዳ አልጋ ላይ ታስተኛዋለች (3/6/2013፣ ገቀ፣ ቃመ)፡፡

ገበታን ሶስት ጊዜ ከፍ ማድረግ ትዕምርታዊ ድርጊት ሲሆን ገበታው የሚወለደውን ህፃን እንዲወክልና ገበታውን ከፍ ማድረግም ልጅ ተወልዶ ማንሳትን እንዲወክል የተደረገ ነው፡፡ ገበታው ከፍ የሚደረገው ሶስት ጊዜ መሆኑ አርጐባዎች ነገር በሶስት ይፀናል ብለው የሚያምኑ በመሆናቸው ምክንያት የህፃኑን በሰላም ተወልዶ መነሳት ማጽናታቸው ነው፡፡ ገበታው ወደ ጓዳ እንዲገባ መደረጉም ልጅ ተወልዶ በጓዳ እንዲገኝ መመኛ ነው፡፡ በንግግር "ልጁ ተወለደ! ልጁ ተወለደ!" ማለትም የህፃኑን በሰላም መወለድ ማምሰያ ነው፡፡ በመሆኑም ሴቶቹ ይህን ድርጊት በማድረግ ነፍሰጡሯ በሰላም ወልዳ ልጇ በጓዳዋ እንዲሆን ያመስላሉ፡፡ በተመሳሳይ ድፍን ቅል አጥቦና በጨርቅ ጠቅልሎ "ወለደች! ወለደች!" በማለት በአልጋ ላይ ማድረግ ትዕምርታዊ ድርጊት ነው፡፡ ቅሉ የሚወለደውን ህፃን እንዲወክል የተደረገ ሲሆን ተወለደ ብሎ ቅሉን እንደ ህፃን አጥቦና አልብሶ አልጋ ላይ ማድረግ ህፃኑ ተወልዶ በጓዳ እንዲገኝ የማምሰያ ትዕምርት ነው፡፡ ገበታ በመያዝ እልል እያሉ ከፍ የማድረግና ወደ ጓዳ የማስገባት፣ ድፍን ቅል አጥቦና አልብሶ እንደ ልጅ አልጋ ላይ የማድረግና ያልተወለደ ልጅን ተወለደ የማለት ትዕምርታዊ ድርጊቶችና ቃላት ነፍሰጡሯ በሰላም እንድትገላገል የማድረግ የክዋኔው ዓላማ ጋር ተሰናስለው የተደረጉና ፍችያቸውም በዚያው አግባብ የሚለይ ናቸው፡፡

ሴቶቹም ሆኑ ወንዶቹ ገንፎውን ከበሉ በኋላ እጃቸውን ይታጠቡና እጣቢው ወደ ጓዳ አልጋ ስር ይፈሳል እንጂ በደጅ አይፈስም፡፡ ገንፎው ዱዓ የተደረገበት በመሆኑ በረከት የሚያስገኝ እንደሆነ ይታመናል፡፡ በረከት የሚያስገኝ ነገር ከነፍሰጡሯ ቤት ሳይወጣ እዚያው መቅረቱ ለነፍሰጡሯና ለቤተሰቧ በረከት ያስገኛል ተብሎ ስለሚታመን የተመጋቢዎቹ እጅ እጣቢ እንኳን ወደ ውጭ ወጥቶ ከመደፋት ይልቅ

ጓዳ ውስጥ፣ አሊጋ ስር እንዲፈስ ይደረጋል (ወ/ሮ ሳሱየ አሊየ፣ 6/7/2013፣ አቀ፣ ቃመ)፡፡ በዚህ መልኩ ገንፎው ተበልቶ ካበቃ በኋላ ቡና ይጠጣና ሴቶቹ ዝኪር ያደርጋሉ፡፡ ዝኪር በአንድ አውራጅና ቁጥራቸው ብዙ በሆነ ተቀባዮች የሚከወን ማሞገሻና መማጠኛ ነው፡፡ ዝኪሮቹ ከተከወኑ በኋላ የስነ ስርዓቱ ክዋኔ ማብቂያ በመሆኑ የመጨረሻ ዱዓ ተደርጐ ተጠሪዎች ወደየቤታቸው ይሄዳሉ (17/2/2013፣ ጋቀ፣ ም፤ 11/3/2013 እና 25/3/2013 ላመቀ፣ ም)፡፡ ከአምሮት ክዋኔ በኋላ የነፍሰጡሯ እናት፤ እናት በህይወት ከሌለች እናትን ወክላ የመጣችው ሴት ነፍሰጡሯን በቀሪው የነፍሰጡርነት ጊዜዋ ለመንከባከብና ስትወልድም ለማረስ እዚያው ቤት ትቀራለች ወይም ነፍሰጡሯን ወደ ራሷ ቤት ይዛት ትሄዳለች (ወ/ሮ ሳሱየ አሊየ፣ 6/7/2013፣ አቀ፣ ቃመ)፡፡

### 5.1.4. የወሊድ ዝግጅት

ነፍሰጡር የወሊድ ዝግጅት የምታደርገው ሰባት ወር ሲሆናት ጀምሮ ነው፡፡ ነፍሰጡር ሰባት ወር ሲሆናት ጀምራ ከምታደርጋቸው ዝግጅቶች መካከል አንዱና ዋናው የምግብ ግብዓቶችን ማዘጋጀት ነው፡፡ በዚህ ጊዜ ነፍሰጡሯ ወልዳ በምትተኛበት ጊዜ የምትመገበውና እንግዳ የሚሸኝበት የምግብ ግብዓት ይዘጋጃል፡፡ በመሆኑም ጤፍ፣ ማሽላ፣ ገብስ፣ ቅቤ፣ ማር፣ ዶሮ፣ በርበሬ፣ ሽሮና ተልባ ከገበያ የሚገዛው ተገዝቶ፤ ከቤት በግብርና ስራ የሚገኘውም ተዘጋጅቶ ለነፍሰጡሯ የአራስነት ጊዜ ተብሎ ይቀመጣል፡፡ ቅቤው ተነጥሮ፣ ሽሮና በርበሬው ተፈጭቶ፣ ገብሱ ተፈትጐና ደርቆ ይቀመጣል (ወ/ሮ አሚና ኢብራሂም፣12/2/2013፣ ጋቀ፣ ቃመ)፡፡ በአርጐባዎች ዘንድ የአራስ ሴት ዋና የመታረሻ ምግብ ከዶሮ ስጋ የሚዘጋጅ በመሆኑ ነፍሰጡሯ በነፍሰጡርነት ጊዜዋ ቀደም ብላ ዶሮ ማርባት ትጀምራለች ወይም ከገበያ ገዝታ እስከምትወልድበት ጊዜ ድረስ እየተንከባከበች ታቆያለች (ወ/ሮ መራኢና መሐመዴ፣ 22/3/2013፣ ላመቀ፣ ቃመ)፡፡

ሌላው ዝግጅት ነፍሰጡሯ የምትወልድበትን ቤትና መኝታዋን የማሰናዳትና የማጽዳት ስራ ነው፡፡ የነፍሰጡር ቤት ብርሀን የሚያስገባ ቀዳዳ ካለው ቀዳዳው ሁሉ እየተጠቀጠቀ፤ ግድግዳውና ወለሉ በከብት አዛባ እየተለቀለቀ ይስተካከላል፡፡ ነፍሰጡር በቤት ውስጥ ስትወልድ የምትወልደው በጠፍር በተሰራ ድንክ አልጋ ላይ በመሆኑ ድንክ አልጋው በቤቷ ካላት አጽድታ ለመውለጃዋ አዘጋጅታ ታስቀምጠዋለች፡፡ ድንክ አልጋ በቤቷ ከሌለ ደግሞ ከጐረቤት ተውሳ አጽድታ ታስቀምጣለች፡፡ ከዚያ በኋላ ቤቷንና የምትወልድበትን ቦታ ታፀዳለች፤ ሽታ[25] ታዘጋጃለች፤ ሽታ በማጨስ የምትወልድበት ቤትና አካባቢ ጥሩ መዓዛ እንዲኖረው ታደርጋለች፤ ልብሶቿ እንዲታጠቡና ንፁህ እንዲሆኑ፣ ከዚያም ሽታ እንዲሞቁ ታደርጋለች፡፡ ነፍሰጡሯ ከወለደች በኋላ የምትሞቀው የወይባና የአዝጋሮ ግንድ አስፈልጣ፣ ሳሙናና ሽቶ ገዝታ ታስቀምጣለች፤ ስትወልድና ወልዳ ስትተኛ የምትለብሰውን እና የህፃኑን ልብስም ታዘጋጃለች (ወ/ሮ ጦይባ ይማም፣ 5/10/2012፣ ጋቀ፣ ቃመ)፡፡

---

[25] ጥሩ መዓዛ ያለው ጭስ ነው፡፡

ነፍሰጡሯ ዘጠኝ ወሯ ከገባ በኂላ በዋናነት ቀደም ሲል የቀረቡ የምግብ ግብዓቶችን የማሰናዳት ስራ የሚከናወን ሲሆን በወሊድ ወቅት የሚያስፈልጉ ምላጭና ማተቢያ ማግ አዘጋጅቶ ማስቀመጡም ሌላው ስራ ነው፡፡ ነፍሰጡሯ ከእነዚህ ከወሊድ በፊት የሚከናወኑ ስራዎች ውስጥ ቀለል ያሉትን የምታከናውን ሲሆን ሌሎች ስራዎችን ከአምሮት ስነ ስርዓት ክዋኔ በኂላ አጠገቧ የሆነችው እናቷ ወይም ሌላ የቤተሰቧ አባል የሆነች ሴት እና ጐረቤቶቿ ይሰሩላታል፡፡ በዚህ ጊዜ የባል ሚና በዋናነት በግብርና ስራ የሚገኙትን ማቅረብና የሚገዙትንም ገንዘብ በመስጠትና ገበያ ሄዶ በመግዛት እንዲሟሉ ማድረግ ነው (ወ/ሮ አሚና ኢብራሂም ፣12/2/2013፣ ጋቀ፣ ቃመ)፡፡

ነፍሰጡሯ የመውለጃዋ ቀን ሲቃረብ ስጥቂት የሚባል የብሔረሰቡን ባህላዊ የፀጉር ስሪት ትሰራለች፡፡ ስጥቂት ከመካከል ተከፍሎ ወደ ጐንና ወደ ኂላ ጥቅጥቅ ተደርጐ የሚሰራ የፀጉር ስሪት ነው፡፡ ነፍሰጡር አንድ ጊዜ ፀጉሯን በዚህ መልክ ከተሰራች በኂላ ወልዳ የአራስነት ጊዜዋን ጨርሳ በወለደች አርባኛ ቀን የግዴታ እጥበት እስከምታደርግበት አርባኛ ቀን ድረስ ፀጉሯን አትፈታም፤ አትታጠብም፡፡ ነፍሰጡሯ ፀጉሯን ከተሰራች በኂላ በተደጋጋሚ ፀጉሯን ቅቤ እየተቀባች ፀጉሯ ጥሩ መዓዛ እንዲኖረው ማታ ማታ ፀጉሯን ብቻ አዝጋሮ ታሞቃለች (ወ/ሮ አሚና ኢብራሂም፣ 12/2/2013፣ ጋቀ፣ ቃመ)፡፡

ነፍሰጡር ሴት የመውለጃዋ ጊዜ ሲደርስ ፀጉሯን ሹሩባ መሰራቷና ሹሩባው ነፍሰጡሯ ከወለደችም በኂላ በአራስነት ጊዜዋ ሁሉ የሚቆይ መሆኑና በአርባኛ ቀን የሚፈታ መሆኑ ትዕምርታዊ ድርጊት ነው፡፡ ፀጉር ሲሰራ መበጠሩ፣ መፍታታቱ፣ መናፈሱ ይቀርና በሹሩባ መልክ ይቋጠራል፤ ይታሰራል፡፡ በአንፃሩ ደግሞ አራስ የአራስነት ጊዜዋ እንደ ፍላጐቷ የማትሆንበት፣ ከእለት ተእለት የስራ እንቅስቃሴዋ የምትለይበት፣ ወደ ውጭ በፈለገችው ሰዓት የማትወጣበት፣ ከነፋስና ከመገለጥ የምትጠበቅበት ጊዜ ነው፡፡ በተጨማሪም የአራስነት ጊዜ ማብቂያ ወላዷ በወለደች አርባኛ ቀን ሲሆን ወላዷ ከዚያ በኂላ የአራስነት ጊዜዋ አብቅቶ በመጠኑም ቢሆን ወደ እለት ተእለት ህይወቷ የምትመለስበት፣ ወደ ውጭ ለመውጣት በሰዓት የማትወሰንበት፣ ነፋስ ነካሽ የማትባልበትና ነፃ የምትሆንበት ጊዜ የሚጀምርበት ነው፡፡ ስለሆነም የፀጉር ስራው ወይም ሹሩባው አራስ ላለባት የመጠበቅና እንደፈቀደች ያለመሆን ሁኔታ፣ የአራስነት ጊዜ ማብቃቱን ተከትሎ መፈታቱ ደግሞ የአራሷን መፈታትና ነፃ መሆንን በትይዩነት የሚያሳይ ትዕምርታዊ ድርጊት ነው፡፡

በቅድመ ወሊድ ጊዜ የሀይማኖት አባቶች ዱዓ በማድረግ ትልቅ ሚና አላቸው፤ በአምሮት ስነ ስርዓት ላይ ዱዓ ያደርጋሉ፣ ምጥ በሚጠነክርበት ጊዜም ሰለዋት[26] ይላሉ (አቶ መሐመድ አቡበከር፣ 2/2/2013፣ ጋቀ፣ ቃመ)፡፡

በዚህ የመለየት ጊዜ ነፍሰጡሯ በተለየ ትታያለች፤ የስጋና የጋብቻ ዘመዶቿና ጐረቤቶቿ ከሌላው ሰው በተለየ ያምራታል፣ ይሸታታል በማለት በተለየ ምግብ

[26] የእስልምና ሐይማኖት ፀሎትና ስግደት

ይንከባከቢታል፤ የቤት ውስጥ ስራዎቿን እየሰሩ ወይም እያገዙ ይንከባከቢታል፤ ነፍሰጡር ከሌላው ሰው በተለየ በሰው ዓይንና በእርኩስ መንፈስ ምክንያት ለሚመጡ ህመሞች የተጋለጠች ነች ተብሎ የሚታመን በመሆኑ ሰዎች አይናቸውን ሰበር አድርገው እንጂ አተኩረው አያዩዋትም፤ ነፍሰጡር በመንገድ ስታጋጥም "እንትፍ እንትፍ" ይባላል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ነፍሰጡር በምግብ፣ በአረማመድ፣ በአቀማመጥ፣ በአተኛኘት፣ በድርጊትና እንቅስቃሴ ክልክሎች ያሉባት መሆኑና እነዚህንም አስመልክቶ ምክር የሚሰጣት መሆኑ በአርጉባዎች ልማድ ነፍሰጡር ከነበረችበት ቡድን መለየቷን የሚያሳዩ ሁኔታዎች ናቸው፡፡

## 5.2. ሽግግር

ነፍሰጡሯ የመውለጃዋ ጊዜ ደርሶ ምጥ ከጀመራት ጊዜ ጀምሮ እስከ አርባ ቀን እጥበቷ ዋዜማ ድረስ ያለው ጊዜ የሽግግር ጊዜ ነው፡፡ ይህ ጊዜ የወሊድ፣ የላንቃ ማንሳት፣ የደም ዶሮ እርድና የልጅ ጓሮ ቀበራ ስነ ስርዓቶች፣ የአራስ እንክብካቤና ጥየቃ እና የሰባት ቀን እጥበት ስነ ስርዓት የሚከወኑበት ነው፡፡

### 5.2.1. የወሊድ ስነ ስርዓት

በአሁኑ ጊዜ በአካባቢው ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተሻሻለና እየተስፋፋ በመጣው ዘመናዊ የህክምና አገልግሎትና ይህን ተከትሎ በሚደረገው የግንዛቤ ማስጨበጥ ስራ በቤት ውስጥ የመውለድ አማራጭ ብቻ የነበራቸው እናቶች ወደ ጤና ተቋማት በመሄድ ይወልዳሉ፤ ቅድመ ወሊድ ክትትልም ያደርጋሉ፡፡ ነገር ግን ይህን የሚያደርጉት ሁሉም እናቶች አይደሉም፡፡ በመስክ ስራ ወቅት ከልምድ አዋላጆች አቅም በላይ የሆነ ችግር አጋጥሞ ወደ ጤና ተቋማት ለመሄድ ካልተገደዱ በስተቀር በቤታቸው በልምድ አዋላጅ እየታገዙ መውለድ የሚፈልጉ ብዙዎች መሆናቸውን ለማስተዋል ተችሏል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በጋቾኔ ጤና ጣቢያ ወላዶች በተቋሙ ለመውለድ እንዲነሳሱ ለማድረግ በባህላዊ መንገድ የተሰራ የወላዶች ማረፊያ ጐጆ ከታሰበለት ዓላማ ውጭ ግምጃ ቤት መደረጉን በምልከታ ለመታዘብ ተችሏል፡፡ ከዚህ በታች የአርጉባዎች ባህላዊ የወሊድ ስነ ስርዓት ክዋኔ ቀርቧል፡፡

ነፍሰጡሯ የምትወልድበት ቀን ደርሶ የህመም ስሜት ሲሰማት በአካባቢው የምትገኝ የልምድ አዋላጅ ትጠራለች፡፡ ምጥ እግር አይወድም፤ ይመለሳል የሚል እምነት ያለ በመሆኑ ምክንያት የወሊድ ስነ ስርዓት በሚከናወንበት ቤት ውስጥ ከልምድ አዋላጅና ከቤተሰብ አባላት ውጭ ያሉ ሰዎች እንዲሰበሰቡና ሰው እንዲበዛ አይፈለግም፡፡ ነገር ግን ጐረቤቶች የወሊድ ስነ ስርዓት ባለበት ቤት የሚገኙ ከሆነ ይህ በሁለት ምክንያቶች ሊሆን ይችላል፡፡ አንደኛው ምክንያት የወላዷን ምጥ የሰማች የቅርብ ጐረቤት ለሌሎች አሰምታ ከሆነ ሲሆን ሁለተኛው ምክንያት የወላዷ ምጥ ሲጠነክር ሰዎች ዱዓ እንዲያደርጉ ተጠርተው ከሆነ ነው (ወ/ሮ ኢና ሙጋ፣ 10/3/2013፣ ላመቀ፣ ቃመ)፡፡

በአርጐባዎች ባህል መሰረት አንዲት ሴት የምትወልደው በጓዳ ውስጥ ሲሆን የምትኖርበት ቤት ክፍል አንድ ብቻ ከሆነ እዚያው ክፍል ውስጥ ተጋርዶ ትወልዳለች፡፡ የምትወልደው ፍራሽ በሌለው ድንክ አልጋ ላይ ሲሆን ስትወልድ የሚኖረው ፈሳሽና ስትታጠብ የሚፈሰው ውሃ ቤቱን እንዳያበላሽ ከአልጋው ስር ጉድጓድ ተቆፍሮ ይዘጋጅና ከወለደችና ከታጠበች በኋላ አፈሩ ተመልሶ ጉድጓዱ ይደፈናል (ወ/ሮ ኢና ሙጋ፣ 10/3/2013፣ ላመቀ ቃመ)፡፡

በወሊድ ጊዜ ነፍሰጡሯ በሁለት መልኩ ልትሆን ትችላለች፡፡ አንደኛው በቀኝ ወይም በግራ ጐኗ ተኝታ፤ የልምድ አዋላጃE ደግሞ ከግርጌ ሆና እየረዳቻትና ከራስጌ አንድ ሌላ ሴት እየደገፈቻት፤ ስትወልድ ደግሞ ሌላ ሴት ከላይ ያለውን እግሯን ከጉልበቷ ከፍ በማድረግ ይዛ የምትወልድበት ሁኔታ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ አልጋው ላይ ድንጋይ ተደርጐና እዚያ ላይ ጨርቅ ተደልድሎ ወላዷ እዚያ ላይ ቁጭ ብላ፤ የልምድ አዋላጇ ከግርጌ ሆና፤ ሌላ ሴት ከጀርባዋ በኩል ሆና ትከሻዋንና ወገቧን በመደገፍ የምትወልድበት ነው፡፡ በጀርባ መተኛት ጽንሱን ወደ ታች ከመምጣት ይልቅ ወደ ላይ ከፍ ያደርገዋል፤ እትብቱ በጽንሱ አንገት ላይ እንዲጠመጠም ያደርጋል ተብሎ ስለሚታመን ወላድ በጀርባዋ ተኝታ አትወልድም (ወ/ሮ ሞሚና መሐመድ፣ 19/4/2013፣ ጨቀ፣ ቃመ)፡፡

የልምድ አዋላጇ ከግርጌ ቁጭ በማለት የነፍሰጡሯን ሆድ ቅቤ እየቀባች የህመምና የምጥ ሁኔታዋን ትከታተላለች፤ ወላዷ ማድረግ ያለባትንና የሌለባትን እየነገረች ትመክራታለች፤ ወላዷ ትንፋሿን ወደ ውስጥ ማድረግ እንዳለባት፣ ወደላይ ወደላይ መተንፈስ እንደሌለባት፣ መጮህና መጠማዘዝ እንደሌለባት፣ ማማጥ በማይገባት ሰዓት ማማጥ እንደሌለባት ትነግራታለች፡፡ ወላዷ ከላይ በተገለፀው መንገድ ቁጭ ብላ የምታምጥ ከሆነ ድካም ሲሰማት ትንሽ ጊዜ በጐኗ እንድትተኛ ትደረጋለች፡፡ ወላዷ ምጧ ገና ከሆነና አቅም ካላት አልፎ አልፎ እየተነሳች ቤቱ ውስጥ እንድትንቀሳቀስ ትደረጋለች፡፡ ምጧ እየበረታ ሄዶ የእሽርት ውሃ ሲቃረብ ግን ከአልጋ ላይ እንዳትነሳ ትከለከላለች፡፡ የልምድ አዋላጆች የእንሽርት ውሃ መቅረቡን የጽንሱን ግፊት በማጤን ይለዩታል፡፡ ከዚያ በኋላ ወላዷ አልጋው ላይ በመሆን ታምጣለች፤ የልምድ አዋላጇ የህመሙ ስሜት ሲመጣ እንድታምጥና ወደ ታች እንድትጫን፣ ህመሙ ቀለል ሲል ደግሞ ትንፋሽን እንድትሰበስብ ትነግራታለች፡፡ ሌሎች ሴቶችም ድርሻቸውን ለመወጣት ይዘጋጃሉ፡፡ በወሊድ ጊዜ የአንድ የልምድ አዋላጅ መገኘት በቂ ሲሆን ከፍ ሲል እንደተገለፀው ወላዷን የሚደግፉና ወላዷ ከወለደችም በኋላ ወላዷንና ህፃኑን በማጠብ አዋላጃEን የሚያግዙ ሁለት ወይም ሶስት ሴቶች ይኖራሉ (ወ/ሮ ሞሚና መሐመድ፣ 19/4/2013፣ ጨቀ፣ ቃመ)፡፡

ነፍሰጡሯ በምታምጥበት ጊዜ በቤቱ ውስጥ የሞቀ ጨዋታና ጫጫታ እንዲኖር አይፈቀድም፡፡ ጨዋታ በሌለበት ሁኔታ ነፍሰጡሯ ምጧ እንዲገራና በሰላም እንድትገላገል ዱዓ ይደረጋል፡፡ ከዚያ በኋላ ዱዓ ለማድረግ ቡና ይፈላል፡፡ የሚፈላው ቡና ምጥን ያገራሉ ተብለው በሚታመንባቸው ስም ነፍሰጡሯ እስክትወልድ ድረስ እየተደጋገመ ይፈላል፡፡ በቅድሚያ የሚፈላው ቡና የሲቲና ፋጡማ ቡና ተብሎ ነው፡፡

የሚፈላውን ቡና መጀመሪያ ነፍሰጡሯ እንድትጨብጠው ይደረግና በሚቆላበት ምጣድ ላይ ተደርጐ ትንሽ ጊዜ እንዲቆይ ከተደረገ በኋላ ተቆልቶ ከነምጣዱ በወላዷ አልጋ ስር ይገባና ጭሱ እንዲጨስባት ይደረጋል፡፡ ምጥ ሲበረታ ወላዷ ግብር መገበር ያስለመደችው ነገር ግን ያሳለፈችበት አውሊያ ካለ ብር ትጨብጥና የአውሊያውን ስም ጠርታ ከጭንቋ እንዲገላግላት ትለምናለች (ወ/ሮ ነፊሳ አህመድ፣ 16/2/2013፣ ጋቀ፣ ቃመ)፡፡ ወላዷ ቡናውን እንድትጨብጠው ማድረጉና ቡናው ምጣድ ላይ ከተደረገም በኋላ ትንሽ ጊዜ መጠበቁ ትዕምርታዊ ድርጊቶች ናቸው፡፡ ወላዷ ቡናውን ጨብጣ መቆየቷ በስማቸው ቡና የተፈላላቸውን አማላጆች አማልዱኝ፣ እርዱኝ ማለት፣ መለመን፣ መማፀን ሲሆን ቡናውን በምጣድ ላይ አድርጐ መቆየት የአማላጆቹን ምልጃና እርዳታ የመጠበቅ ትዕምርታዊ ድርጊት ነው፡፡ ወላዷ ጭሱ እንዲጨስባት የሚደረገው ቡናው የተፈላው በምጥ አግሪዋ በፋጡማ ስም በመሆኑ ጭሱ ወላዷ ቶሎ እንድትወልድ ይረዳታል በሚል እምነት ምክንያት ነው፡፡ ብሩን ጨብጣ መያዟም ቡናውን እንደመጨበጥ ሁሉ የመማፀን ድርጊት ነው፡፡

ቡናው ፈልቶ ዱዓ ከተደረገ በኋላ ከቡናው ቀድተው መጀመሪያ ለወላዷ ያቀምሷታል፡፡ ቡናው የተፈላው በፋጡማ ስም በመሆኑ መጀመሪያ የተቀዳውን መቅመሷ ምጧን ያገራዋል፣ ቶሎ እንድትወልድ ይረዳታል ተብሎ ይታመናል፡፡ ከዚያ በኋላም በተመሳሳይ መንገድ የነቢዩ ቡና፣ የእማ መዲና ቡና፣ ወዘተ እየተባለ ተፈልቶ መጀመሪያ የተቀዳው ለነፍሰጡሯ እየተሰጣት ይቆያል፡፡ ከዚህ ውጭ ነፍሰጡሯ ሞቅ ያለ ነገር ለምሳሌ፣ ተልባ ተሞቆ፣ አጥሚት በቅቤ ተደርጐ እንድትጠጣ ይደረጋል (ወ/ሮ ነፊሳ አህመድ፣ 16/2/2013፣ ጋቀ፣ ቃመ)፡፡

ምጥ ሲበረታ መፍትሄ ይሆናሉ ተብለው የሚታመንባቸው እምነታዊ ድርጊቶች የሚከወኑ ሲሆን ወንድ ሰው ይገባና የወላዷን እጅ ወይም ራስ ይዞ ቁርዓን ይቀራባታል፤ የተሰበሰቡ ወንዶች ዱዓ ያደርጋሉ፤ ሰለዋት ይላሉ፤ ዱዓ የተደረገበት ጫት ታሽቶ፣ ተጨምቆና በውሃ ተበጥብጦ ይርከፈከፍባታል፤ የቁርዓን ቃል በሉህ[27] ላይ ተጽፎ ይታጠብና እንድትጠጣው ይደረጋል፤ ለጋ ቅቤ ቀርቦ ሁሉም "እንትፍትፍ" ይሉበትና ሆዷ ይቀባል፡፡ ምጥ የጠናው ወላዷ የሰው ዓይን ህመም ኖሮባትና በምጥ ጊዜ ተነስቶባት ነው ተብሎ ከታመነ ደግሞ ቁርዓን ከመቅራት በተጨማሪ እውቀቱ ባለው ሰው ጽህፈት ተጽፎ በጭኗ ላይ ይታሰራል፤ በአካባቢው የባህላዊ መድኃኒት እውቀት ካላቸው ሰዎችና ከሌሎችም ዘንድ የሚገኝ ከሆነ የአንበሳ ፀጉር ወይም የጉማሬ ቆዳ ይጨሳል (አቶ አደም መሐመድ፣ 4/7/2013፣ አቀ፣ ቃመ)፡፡

ምጥ ሲጠነክር ከሚደረጉ እምነታዊ መሰረት ካላቸው ድርጊቶች በተጨማሪ ወላዷ ጽንሱን ወደ ታች መግፋት ያስችሏታል ተብለው የሚታሰቡ ልማዳዊ ድርጊቶች ይደረጋሉ፡፡ አንደኛው ነፍሰጡሯ ውስጡ ክፍት የሆነ የእሳት ማንደጃ ሸንበቆ ከአንድ

---

[27]ሰሌዳ

በኩል በእጅ ተደፍኖ በትንፋሿ "እፍፍ" እንድትል ማድረግ ነው፡፡ ሁለተኛው ወላዷ እንዲያስነጥሳት ቀይ ሽንኩርት ተከትፎና በእንጀራ ተጠቅልሎ እንድትበላ ማድረግ ሲሆን ይህ የማያስነጥሳት ከሆነ በሶስተኛነት የሽንኩርቱ ልጣጭ እሳት ላይ ተደርጐ ጭሱን እንድትታጠንና እንዲያስነጥሳት ይደረጋል (ወ/ሮ አይከዲጅ መሐመድ፣ 28/3/2013፣ ላመቀ፣ ቃመ)፡፡

ምጥ ተፋፍሞ የእሽርት ውሀ ከፈሰሰ በኋላ ትንሽ ተጠብቆ ልጁ[28] ይመጣል ተብሎ ይታመናል፡፡ በመሆኑም የልምድ አዋላጇ ህፃኑን በጨርቅ ተቀብላ አልጋው ላይ ታስቀምጠውና እትብቱን ትቆርጣለች፡፡ እትብት መጀመሪያ ወደ ህፃኑ ሶስት ጣት ተትቶ በማግ ይቋጠርና ሁለት ጣት ታልፎ ከእናት በኩል እንደገና ታስሮ መካከል ላይ በምላጭ ይቆረጣል፡፡ ከዚያ በኋላ አዋላጇ የእንግዴ ልጁ ተመልሶ ወደ ውስጥ እንዳይገባ ከእናት በኩል ያለውን እትብት በወላዷ ጭን ላይ በማግ ታስረዋለች፡፡ የእንግዴ ልጁ እንዲወርድ ሆዷን እያሸቻት እስኪወርድ ድረስ ትጠብቃለች፡፡ ወላዷ እንደተገላገለች የተሰበሰቡ ሴቶች በሙሉ "አላሀምዱሊላህ" እያሉ ይዘያየራሉ፡፡ የወላዷና የባለቤቷ ዘመዶች የተወለደው ልጅ ወንድ ከሆነ ብዙ ጥይት ይተኩሳሉ፤ ሴት ከሆነች ለወንድ ልጅ የሚተኮሰውን ጥይት ያህል ባይሆንም መተኮሳቸው ግን አይቀርም (ወ/ሮ አይከዲጅ መሐመድ፣ 28/3/2013፣ ላመቀ፣ ቃመ)፡፡

ህፃኑ እንደተወለደ ወላዷ ውሃ እንድትጠጣ ትደረጋለች፡፡ ውሀ የእንግዴ ልጁን "ይገድለውና" ቶሎ እንዲወርድ ያደርገዋል ተብሎ ይታመናል፡፡ ወላዷ ከወለደች በኋላ የእንግዴ ልጁ ከቆየ ወይም መነቅነቅ አስለምዳ ከሆነ ወንድ ሰው እንዲነቀንቃት ይደረጋል፡፡ መነቅነቅ ማለት ወላዷ መሬት ላይ ትወርድና ወገቧ ላይ የሙዳይ ክዳን ተደፍቶና የሚነቀንቃት ሰው ከኋላዋ በመሆን የሙዳዩን ክዳን በእግሩ አጣብቆ በመያዝና እጆቹን በእጅና በእጇ ስር በማስገባት በተደጋጋሚ ወላዷን በመጠኑ ብድግ በማድረግና በመነቅነቅ፤ ከዚያም ወላዷን ወደ መሬት በመልቀቅ የእንግዴ ልጁ እንዲወርድ ለማድረግ የሚተገበር ልማድ ነው (ወ/ሮ አይከዲጅ መሐመድ፣ 28/3/2013፣ ላመቀ፣ ቃመ)፡፡

የእንግዴ ልጅ ቢዘገይ ወላዷ የምትቀምሰውና የምታስረው ባህላዊ መድኃኒት ይሰጣታል፡፡ አቶ አደም መሐመድ እንደገለፁት የመጀመሪያው መድኃኒት የጋሜ ቅጠል ነው፡፡ የጋሜ ተክል ቅጠሉ ተጨምቆና በውሀ ተበጥብጦ እንድትጠጣ ይደረጋል፡፡ ሁለተኛው መድኃኒት መኻርጥ የሚባል ቅጠል ሲሆን በወላዷ ጭን ላይ ይታሰራል፡፡ ሶስተኛው መድኃኒት ጽህፈት ሲሆን በወላዷ ወገብ ላይ ይታሰራል (5/7/2013፣ አቀ፣ ቃመ)፡፡

የእንግዴ ልጁ ሲወርድ አዋላጇ በቅል ትቀበለዋለች፡፡ አንዷ ሴት የእንግዴ ልጁን ለመቅበር ስትወስድ በቅደም ተከተል ህፃኑና ወላዷ በሳሙናና ለብ ባለ ውሃ እዚያው ድንክ አልጋው ላይ ታጥበው ገላቸውን ቅቤ ከተቀቡ በኋላ ታጥቦና ተሞቆ የተዘጋጀውን ንፁህ ልብስ ይለብሳሉ፡፡ አልጋው እዚያው እንዳለ ይታጠብና ሲያበቃ

---

[28] ልጁ፣ ህፃኑ ተብሎ የተገለፀው ሁለቱንም ፆታ የሚገልጽ እንጂ ተባዕት ፆታን ብቻ የሚገልጽ አይደለም፡፡

ከአልጋው ስር ለፍሳሽ ተብሎ የተቆፈረው ጉድጓድ አፈሩ እየተመለሰ ተደፍኖ ወላዷ ከነልጇ አልጋው ላይ ይተኛሉ፡፡ አዝጋሮ[29] በጋቻ ላይ ተደርጐ አልጋው ስር ይጨሳል፡፡ ከዚያ በኋላ አዋላጇ ራሷ ትታጠብና የወላዷ ዘመዶች ቅቤና ሽቶ ይቀቧታል፤ አዝጋሮ ያሞቋታል፡፡ ወላዷ የወለደችበት የቆሸሸ ጨርቅ ወደ ውጭ ይወጣና የወላዷ የቤተሰብ አባል ማለትም እናቷ፣ እህቷ ወይም ባለቤቷ ያጥቡታል (ወ/ሮ አይከዲጅ መሐመድ፣ 28/3/2013፣ ላመቀ፣ ቃመ)፡፡

በአርጐባዎች ዘንድ ወንድ ልጅ ጥቃትን ይመክታል፣ ቢያገባም አባቱ ግቢ ቤት ሰርቶ ጋሻ ሆኖ ይኖራል፣ ይደግፋል፣ ይጦራል በሚል ምክንያት ወንድ ልጅ ሲወለድ ትልቅ ደስታ ይሆናል፡፡ ለወንድ ልጅ መወለድ ትልቅ ቦታ የሚሰጥ በመሆኑ ምክንያት በአምሮትና በጉፍታ[30] ስነ ስርዓት ክዋኔዎች ላይ የሚወለደው ልጅ ወንድ እንዲሆን የመሻት መሰረት ያላቸው ዱዓዎች ይደረጋሉ፡፡ በአምሮት ስነ ስርዓት ላይ "ልጁም ወንድ ይሁን ምጡም ገር ይሁን" (ወ/ሮ አሚና ኢብራሂም፣ 17/2/2013፣ ጋቀ፣ ም) እና "ወንዱን! ወንዱን! ወንዱን! ምጡ እማይጠናውን [ይስጣት]" (ወ/ሮ በድሪያ መሐመድ፣ 17/2/2013፣ ጋቀ፣ ም) ተብሎ ዱዓ ሲደረግና በጉፍታ ስነ ስርዓት ክዋኔ ላይም "የወንድ ልጅ እናት አላህ ያርጋት" (አይኔ ይማሙ፣ 23/5/2013፣ ገቀ፣ ም) ተብሎ ዱዓ ሲደረግ በምልከታ ለመታዘብ ተችሏል፡፡

### 5.2.2. ላንቃ ማንሳት

ህፃኑ ከተወለደ በኋላ ላንቃው ይነሳል፡፡ ላንቃ ማንሳት ማለት ህፃኑ ሲወለድ በጣት ትንሽ ማር በመቆንጠር የህፃኑን ላንቃ ወደ ላይ ማሸት ሲሆን ይህ የሚደረገው ህፃን ሲወለድ ላንቃው ወደ ታች የወረደ ነው ተብሎ የሚታመን በመሆኑ፤ በዚህ መልኩ ላንቃው ካልተነሳ ወደፊት ትንታ ያጠቃዋል፣ ሲያወራ ይነፋነፋል፣ ጥሩ ድምጽ አይኖረውም ተብሎ ስለሚታመን ነው (አሚና ኢብራሂም፣ 12/2/2013፣ ጋቀ፣ ቃመ)፡፡

### 5.2.3. የደም ዶሮ እርድ

ወላዷና ህፃኑ እንደተኙ ወዲያው ዶሮ ታርዶ አልጋው ስር ጣል ይደረጋል፡፡ የእርዱ ዓላማ ደም እንዲፈስ በማድረግ ወላዷንና ህፃኑን ከእርኩስ መንፈስ መጠበቅ ሲሆን የደም ዶሮ ይባላል፡፡ እርኩስ መንፈስ ደም የፈሰሰበትን ቦታ ይወዳል፣ ደም የፈሰሰውን ሰው ህመም ላይ ይጥላል ተብሎ የሚታመን በመሆኑ ቶሎ ዶሮ አርዶ ደም በማፍሰስ ወላዷ በፈሰሳት ደም ፋንታ እንዲሆን ወይም ጭዳ እንዲሆን ይደረጋል፡፡ ወላዷ በፈሰሳት ደም ምክንያት በእርኩስ መንፈስ ጉዳት እንዳይደርስባት የዶሮው ደም ይከላከልላታል ተብሎ ይታመናል (አሚና ኢብራሂም፣ 13/2/2013፣ ጋቀ፣ ቃመ)፡፡

---

[29] ጥሩ ጠረን ያለው፣ ግንዱ ተፈልጦ ቤት ውስጥ የሚጨስ፣ ያገባች ሴት የምትሞቀውና ልብሷንም የምታሞቅበት ተክል

[30] በሰርግ ቀን ሙሽራዋ በራሷ ላይ የሚታሰርላትና ባለትዳር መሆኗን የሚገልጽ ሻሽ ሲሆን ስነ ስርዓቱ ይህን ሻሽ የማሰር ስነ ስርዓት ነው፡፡

### 5.2.4. የልጅ ጓሮ ቀበራ

የልጅ ጓሮ የእንግዴ ልጅ ነው፡፡ የእንግዴ ልጅ በቅል ተደርጐ ይቀበራል፡፡ የእንግዴ ልጁ መቀበሩና ሲቀበርም በቅል መሆኑ የእንግዴ ልጅ ክብር የሚሰጠው በመሆኑ ምክንያት ነው፡፡ የእንግዴ ልጅ ህፃኑ ከመወለዱ በፊት ህይወት የሚያገኝበት፣ ነፍስና እንቅስቃሴ የነበረው ነው ተብሎ የሚታመን በመሆኑ እትብት ተቆርጦ ቀሪው የእንግዴ ልጅ እስኪወጣ ድረስ በወላዷ ጭን ላይ የሚታሰረው እንግዴ ልጁ ህይወትና እንቅስቃሴ ስላለው ወደታች መውረድ ሲገባው ወደላይ እንዳይወጣ ነው፡፡ በመሆኑም ከህፃኑ ጋር የነበረ ነፍስ የነበረው ነገር እንዲሁ በአፈር ላይ አይጣልም፤ ህፃኑ በጨርቅ ሲነሳ የእንግዴ ልጁ በቅል ተደርጐ ይቀበራል ወ/ሮ ኢና ሙጋ፣ 10/3/2013፣ ላመቀ፣ ቃመ)፡፡

የእንግዴ ልጅ የሚቀበረው የተወለደው ህፃን ወንድ ከሆነ በቤት ውስጥ፣ ሴት ከሆነች ደግሞ ከቤት ውጭ ሲሆን ወ/ሮ ኢና ሙጋ፣ 10/3/2013፣ ላመቀ፣ ቃመ) ይህም ድርጊት ትዕምርታዊ ነው፡፡ በአርጐባ ባህል ወንድ ልጅ አድጐ ትዳር ሲይዝ ኑሮውን የሚያደርገው በቤተሰቡ መኖሪያ ቅጥር ግቢ መኖሪያውን በመስራት ሲሆን ሴት ልጅ አድጋ ስታገባ ግን የምትኖረው ወደ ባሏ አካባቢ በመሄድ ነው፡፡ በመሆኑም ወንድ ልጅ ሲወለድ የእንግዴ ልጁ በቤት ውስጥ የሚቀበረው ህፃኑ አድጐ በትክክልም ኑሮውን በቤተሰቡ አካባቢ እንዲያደርግ፣ የቤተሰቡን አካባቢ ይዞና አስከብሮ እንዲኖር ማምሰል ሲሆን ሴት ልጅ ስትወለድ የእንግዴ ልጁ ከቤት ውጭ የሚቀበረው ህፃኗ አድጋ ቶሎ ትዳር እንድታገኝና ወደ ባሏ አካባቢ እንድትሄድ ማምሰያ ነው፡፡

### 5.2.5. የአራስ ቤት ገጽታና እንክብካቤ

አብዛኛውን ጊዜ አንዲት ሴት የመጀመሪያ ልጃEን ስትወልድ የምትታረሰው በቤተሰቧ ቤት፤ በእናቷ እጅ ነው፡፡ እናት በህይወት ባትኖር እንኳን እህቶች፣ አክስቶች ወይም የእንጀራ እናት ስለሚኖሩ በቤተሰቧ ቤት ወልዳ ትታረሳለች፡፡ ሁለተኛ እርግዝና ሲሆን ግን እንደ ወላጇ ፍላጐት በቤተሰቧ ቤት አልያም በባሏ ቤት ትወልዳለች (ወ/ሮ ሶሀሊየት ኑሬ፣ 7/4/2013፣ ጨቀ፣ ቃመ)፡፡ ለአራስና አዲስ ለተወለደ ህፃን የሚደረግን እንክብካቤ በሁለት መክፈል የሚቻል ሲሆን እነዚህም በምግብና በንጽህና መንከባከብና ለተለያዩ ህመሞች እንዳይጋለጡ ማድረግ ናቸው፡፡

### ሀ. የአራስና የህፃን ምግብና ንጽህና አጠባበቅ

አራስ በአራስነት ጊዜዋ ጥሩ ጥሩ ምግቦች እየተዘጋጁላት እንድትመገብ ትደረጋለች፡፡ ለአራስ የሚዘጋጁ ዋና ዋና ምግቦች ዶሮ፣ አሊጣጦ፣ በቅቤ የታሸ ቂጣ፣ ገንፎ፣ አጥሚትና ተልባ ናቸው፡፡ አራስ በአርባ ቀን የአራስነት ጊዜዋ በብዛት ከዶሮ የሚዘጋጅ ምግብ ይዘጋጅላታል፡፡ አራስ ቢያንስ በቀን አንድ ዶሮ የሚታረድላት ሲሆን ጥሩ የኢኮኖሚ አቅም ባለው ቤተሰብ ውስጥ ያለች አራስ ደግሞ በቀን ሁለት ዶሮ ታርዶላት እንድትመገብ ይደረጋል (ወ/ሮ ሶሀሊየት ኑሬ፣ 7/4/2013፣ ጨቀ፣ ቃመ)፡፡

ጥሩ የሚባል ኑሮ ባለው ቤተሰብ ውስጥ ያለች አራስ በቀን አምስት ጊዜ የምትመገብ ሲሆን መጀመሪያ ጠዋት ገንፎ ተገንፍቶ ትመገባለች፤ ረፋድ ሲል ዶሮ ይታረድና እስኪዘጋጅ ቂጣ ተጋግሮና በቅቤ ታሽቶ ቀርቦላት ትመገባለች፤ ምሳ፣ መክሰስና እራት የተዘጋጀውን ዶሮ በአሊጣጦ ወይም በእንጀራ ትመገባለች፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አጥሚት ተሰርቶላት ትጠጣለች፤ ተልባ ተሞቆ ወይም ለብ ባለ ውሃ ተበጥብጦ ይቀመጥና በመሀል በመሀል ትጠጣለች፡፡ የኑሮ ጫና ባለበት ቤተሰብ ውስጥ ያለች አራስም በተቻለ አቅም ከሌላው በተለየ የአራስ ምግብ ተዘጋጅቶላት ትታረሳለች፡፡ አራስ ሰው ያየውን ምግብ አትመገብም፤ የምትመገበውም ለብቻዋ ነው (ወ/ሮ ሶሀሊየት ኑሬ፣ 7/4/2013፣ ጨቀ፣ ቃመ)፡፡

አራስ በአራስነት ጊዜዋ እንዳትመገባቸው የሚከለከሉ ምግቦች አሉ፡፡ እነዚህ ምግቦች ጥራጥሬ፣ ጐመን፣ ቃሪያ፣ እንዲሁም ረጃ (ሁለተኛ ቡና) እና ጀሚ (ሶስተኛ ቡና) ናቸው፡፡ ጥራጥሬና ጐመን ጡት ለሚጠባው ህፃን ቁርጠት ያመጣበታል፤ ቃሪያ ህፃኑን ያቃጥለዋል፤ ረጃና ጀሚ መጠጣት ደግሞ ህፃኑ ለመሽናት እንዲቸገር ያደርገዋል የሚሉ ምክንያቶች የክልከላዎቹ መነሻዎች ናቸው፡፡ የህፃኑን ምግብ በተመለከተ ህፃኑ ጡት ይጠባል፤ ለጋ ቅቤም እንዲውጥ ይደረጋል፡፡ አንዳንድ ጊዜ የእናት ጡት ወተት ሲቀንስ ወይም ከመጀመሪያውም መጠኑ ትንሽ ሲሆን ከሚውጠው ቅቤ በተጨማሪ የላም ወተት ሁለት እጅ ውሃ እየተጨመረበት እንዲጠጣ ይደረጋል፤ የፍየል ወተትም ይሰጠዋል (ወ/ሮ ፋጡማ ቡሴሂሪ፣ 13/4/2013፣ ጨቀ፣ ቃመ)፡፡

አራስና አካባቢዋ ንፁህና ጥሩ መዓዛ እንዲኖራቸው ይደረጋል፡፡ በመሆኑም አራስ በቀን አንድ ወይም ሁለት ጊዜ ገላዋን ታጥባ አዝጋሮና ሽታ ትሞቃለች፤ ልብሷ በየጊዜው እየታጠበ በአዝጋሮና በሽታ ይሞቃል፡፡ የአራስ ቤትና አራስ የምትተኛበት አልጋ ስር ሁሉ እየተጠረገ አዝጋሮና ሽታ ይጨስበታል፡፡ ህፃኑ በቀን አንድ ጊዜ ወይም ጠዋትና ማታ ሁለት ጊዜ ገላው ታጥቦ ለጋ ቅቤ ጭንቅላቱንና ገላውን ይቀባል፡፡ አራስ በተቻለ መጠን እንድትተኛና እረፍት እንድታደርግ ይደረጋል (ወ/ሮ መርሻዬ አሕመድ፣ 14/4/2013፣ ጨቀ፣ ቃመ)፡፡

ነፍሰጡር ሴት ከመውለዷ በፊት የምትወልድበትን ቤትና አካባቢ በንጽህና መያዟ፣ ከወለደችም በኋላ የሚያርሷት ሴቶች አራሷን፣ ልብሷንና መኝታዋን በንጽህና መያዛቸው ለወላዷ ጤና መጠበቅ ትልቅ አስተዋጽኦ አለው፡፡ ከወሊድ በፊትና ከወሊድም በኋላ ወላድ ሴትን በጥሩ ምግብ መንከባከብ ወላዷ የተመጣጠነ ምግብ እንድታገኝና ጤናዋ እንዲጠበቅ ያግዛል፡፡

### ለ. የአራስና የህፃን ጤና አጠባበቅ

አራስና ጨቅላ ህፃን ለሰው ዓይን ህመም ተጋላጭ ናቸው ተብሎ የሚታመን በመሆኑ በአራስ ቤት አራሷን ከሚንከባከቧት የቅርብ የቤተሰብ አባላት ውጭ ሌሎች ሰዎች አራሷንም ሆነ ህፃኑን እንዲያዩዋቸው አይፈለግም፡፡ ሁለቱንም ከሰው ዕይታና ከነፋስም ለመጠበቅ ሲባል የወይባ ዛፍ ቅርንጫፎ ከነቅጠሉ ተቆርጦ አራሷ

በምትተኛበት አልጋ ዙሪያ ተገድግዶ ትንሽ በር ብቻ ይተዋል፡፡ አራሷን ለመጠየቅ የሚሄዱ ሰዎች አራሷንና ህፃኑን ሳያዩ በተረፈው በር በኩል እጃቸውን እየዘረጉ ብቻ እጇን በመጨበጥ ሰላምታ ይሰጧታል፤ ይጠይቋታል (ወ/ሮ መርሻዬ አሕመድ፣ 14/4/2013፣ ጨቀ፣ ቃመ)፡፡

ህፃን ልጅ ገና ሲወለድም ለሰው ዓይን መከላከያ እንዲሆነው ባህላዊ መድኃኒት እንዲቀምስ ይደረጋል፡፡ የሚቀምሰው አንደኛው መከላከያ ሬት፣ ሁለተኛው የድንጋይ ሙጫ የሚባል በዱር ድንጋይ ላይ የሚገኝ ፈሳሽ ሲሆን ሶስተኛው ተጨቅጭቆ በውሀ የተበጠበጠ የተከዜ ዛፍ ስር ነው፡፡ ህፃን እንደተወለደ እነዚህን ከቀመሰ ለሰው ዓይን ህመም አይጋለጥም ተብሎ ይታመናል፡፡ ህፃኑ በሰው ዓይን እንደታመመ ከተጠረጠረ ደግሞ መድኃኒት የሚሆን ጽህፈት በአንገቱ ላይ ይታሰርለታል፤ ህሞ በሚባል ቅጠል ሰውነቱን ማጠብም ህፃኑ ተረጋግቶ እንዲተኛ ያደርገዋል፡፡ አንድ ህፃን በሰው ዓይን እንደታመመ የሚያስጠረጥሩ ህፃኑ የሚያሳያቸው ምልክቶች አዘውትሮ ማልቀስ፣ ተረጋግቶ አለመተኛት፣ ጡት አለመጥባት፣ ወዘተ ናቸው (አቶ አደም መሐመድ፣ 4/7/2013፣ አቀ፣ ቃመ)፡፡

በነፍሰጡርነት፣ በወሊድና ከወሊድም በኋላ ባለ ጊዜ ሊከሰት ይችላል ተብሎ ለሚፈራ ህመም መከላከያ እንዲሆን፤ ህመሙ ከተከሰተም በኋላ መዳኛ እንዲሆን ባህላዊ ህክምና መተግበሩ ለነፍሰጡሯ ወይም ለአራሷ ከክፉ መንፈስና ከህመም ተጠብቂያለሁ፣ ተከልያለሁ የሚል አእምሯዊ እረፍት ያስገኝላታል፤ ጤናን ከማስገኘት አንፃርም ፋይዳ አለው፡፡

አራስና ጨቅላ ህፃን ከሰው ዓይን በተጨማሪ ለእርኩስ መንፈስ ጥቃት የተጋለጡ ናቸው ተብሎ የሚታመን በመሆኑ በእርኩስ መንፈስ ምክንያት ለህመም እንዳይጋለጡ ጥንቃቄ ይደረግላቸዋል፡፡ እርኩስ መንፈስ ብረት አይወድም፣ ይሸሻል ተብሎ ስለሚታመን እርኩስ መንፈስን ለመከላከል በአራስ መኝታ ላይ ከራስጌዋ ብረት ወይም መሳሪያ ይቀመጣል፣ ለሽንት ስትወጣም ብረት ትይዛለች፤ ፀጉሯ ላይ መርፌ ቁልፍ ወይም ቀለበት፣ በጆሮዋ ላይም ከብር የተሰራ ጌጥ ታደርጋለች (ወ/ሮ ከድጃ መሐመድ ሰዒድ፣ 4/5/2013፣ ገቀ፣ ቃመ)፡፡

እርኩስ መንፈስ እንዳይጠጋትና ምች እንዳይመታት በሚል ምክንያት አራስ ለሽንት የምትወጣው ጠዋት ፀሀይ ከመውጣቱ በፊትና ማታ ጀምበር ከገባች በኋላ ብቻ ነው፡፡ አራስ ለሽንት ወጥታ ስትመለስ ልብሷን በምድጃ እሳት ላይ ሶስት ጊዜ አራግፋ ወደ አልጋዋ ትሄዳለች፡፡ ይህን የምታደርገው ስትወጣ ለበሽታ የሚያጋልጥ እርኩስ መንፈስ ልብሷን ነክቶት ከሆነ መንፈሱን ከላይዋ ለማላቀቅ፣ ለማቃጠል ነው፡፡ በተጨማሪም ለህመም ይዳርጋታል በሚል ምክንያት አራስ በአራስነት ጊዜዋ ጮክ ብሎ ማውራት አይፈቀድላትም (ወ/ሮ ከድጃ መሐመድ ሰዒድ፣ 4/5/2013፣ ገቀ፣ ቃመ)፡፡ ምልከታ በተደረገባቸው የአራስ ቤቶችም ይህን ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

### 5.2.6. አራስ ጠያቂዎች

አራስን ዘመድ አዝማድ፣ ወዳጅና ጐረቤቶች የአራስ መጠየቂያ በመያዝ ይጠይቋታል፡፡ የአራስ መጠየቂያ ዶሮ፣ እንቁላል፣ ለጋ ቅቤ፣ ወይባ፣ አዝጋሮ፣ ሽቶ፣ ሳሙናና ገንዘብ ናቸው፡፡ ለአራስ የበሰለ ምግብ አይወሰድም፤ አራስም ከውጭ በስሎ የመጣ ምግብ አትመገብም፡፡ የዚህ ምክንያቱ ምግቡ የሰው ዓይን ያረፈበት ስለሚሆን አራሷን ለህመም ይዳርጋል የሚል እምነት ነው (ወ/ሮ ፋጡማ ሁሴን፣ 8/7/2013፣ አቀ፣ ቃመ)፡፡

አራስ የሚጠይቁ ሰዎች ወደ አራስ ቤት ሲገቡ "እንኳን ደስ አለሽ" እያሉ ይገባሉ፡፡ ከዚያ በኋላ የያዙትን የአራስ መጠየቂያ ለአራ ሿ ሰጥተው ይቀመጡና ስለ አራሷና ስለ ህፃኑ ደህንነት በመጠየቅ ከአራ ሿ ጋር ይወያያሉ፡፡ ጠያቂዎቹ የቤተሰብ አባላት፣ ከቅርብ ዘመዶች ወይም ጓደኞች ከሆኑ ትንሽ ቆየት ብለው ከደጅ የመታቸውን ፀሀይ ካበረዱ በኋላ ወደ አራሷ በመሄድ፤ በወይባው ግርዶሽ እጃቸውን በማሾለክ እጇን ጨብጠው ሰላምታ ከሰጧት በኋላ እንደቆሙ ያወያዩዋትና ተመልሰው ወደነበሩበት በመሄድ ቁጭ ብለው በምግብ ይስተናገዳሉ፡፡ ጠያቂዎች ከአራስ ቤት ሲወጡ አራሷን "በሙሉ አላህ ያውጣሽ" ብለው ይሄዳሉ (ወ/ሮ ፋጡማ ሁሴን፣ 8/7/2013፣ አቀ፣ ቃመ)፡፡ የአራስነት ጊዜ አራሷ በቀላሉ ለህመም የምትጋለጥበት እንደሆነ ስለሚታሰብ ጠያቂዎች "በሙሉ አላህ ያውጣሽ" ሲሉ ሙሉ የሚለው ቃል ከጤና አለመጉደልን፤ መውጣት ደግሞ የአራስነት ጊዜን በሰላም ማለፍን፣ መሻገርን፣ መቀላቀልን ይወክላሉ፡፡

ከወሊድ በፊት፣ በወሊድ ጊዜና ከወሊድም በኋላ ወላዷን በጉልበት ማገዝ፣ በምግብ መንከባከብ፣ አራስን መጠየቅ፣ በጋራ መመገብ፣ ወዘተ የሰዎችን ማህበራዊ ኑሮ የማጠናከር ፋይዳ አለው፡፡

### 5.2.7. የሰባት ቀን እጥበት ስነ ስርዓት

ሰባተኛው ቀን አራሷ የምትታጠብበት፣ አቂቃ[31] የሚወጣበት፣ ለህፃኑ ስም የሚወጣበትና ህፃኑ ወንድ ከሆነ ምናልባትም ግርዛት የሚከናወንበት ቀን ነው፡፡

#### ሀ. እጥበት

አራስ በወለደች በሰባተኛው ቀን ከሌላው ቀን እጥበት በተለየ በቅጠላ ቅጠል ትታጠባለች፡፡ ወይባ፣ ጋሜ፣ ህሞ፣ ሰንሰል፣ ትግሪና ጨጮ ቅጠሎች ይሰበሰቡና ውሀው ቢጫ ቀለም እስኪያመጣ ድረስ አንድ ላይ ይቀቀሉና መጀመሪያ በተቀቀለው ቅጠላ ቅጠልና በውሀው እያሹ ያጥቧታል፤ በመቀጠል በውሀና በሳሙና ብቻ ያጥቧታል፡፡ ከዚያ በኋላ ቅቤ ቀብተው የተሞቀ ልብስ ያለብሷትና ምግብ ይቀርብላታል (ወ/ሮ አሚና ኢብራሂም፣ 13/2/2013፣ ጋቀ፣ ቃመ)፡፡

[31] የህፃኑ አባት ልጅ ማግኘቱን የሚመሰክርበት ሀይማኖታዊ ስነ ስርዓት

ከዚያ በኋላ አራሷ የተኛችበት አልጋ ወደ ደጅ ወጥቶ በሙቅ ውሃና በተቀቀለው ቅጠላ ቅጠል ከታጠበ በኋላ ለፀሀይ ተሰጥቶ እንዲደርቅ ይደረጋል፡፡ አልጋው ደርቆ ከገባ በኋላ ዶሮ ታርዶ አልጋው ስር ይጣልና እዚያ እንዲንደፋደፍ ይደረጋል፡፡ ዶሮው ከተነሳ በኋላ አልጋው ስር አዝጋሮና ሽታ ይጨስና አራሷ ከመተኛቷ በፊት የአራሷ እናት፣ እህት ወይም ሌላ የቤተሰብ አባል አስቀድመው አልጋው ላይ በመውጣት ጋደም ብለው ከተነሱ በኋላ አራሷ ከነልጇ አልጋው ላይ ወጥታ ትተኛለች፡፡ ደጅ የቆየና ፀሀይ የመታው ነገር እርኩስ መንፈስ ሊነካው እንደሚችል ይታመናል፡፡ በዚያ እቃ ላይ ያረፈ እርኩስ መንፈስ ደግሞ የነካውን ሰው ለበሽታ ይዳርጋል ተብሎም ይታመናል፡፡ በመሆኑም አራስ ከሌላው ሰው በተለየ እርኩስ መንፈስ ይከታተላታል፤ ለበሽታ ተጋላጭ ነች ተብሎ ስለሚታመን አስቀድሞ ሌላ ሴት አልጋው ላይ ጋደም ብላ እንድትነሳ የሚደረገው ድርጊቱ ሊከሰት የሚችልን በሽታ ማክሸፊያ ተደርጐ በመታመኑ ምክንያት ነው፡፡ ከዚያ በኋላ የአራሷ ልብስ ታጥቦ ሲደርቅ በአጐበር ተደርጐ አዝጋሮና ሽታ ይሞቃል፡፡ በዚህ እለት ቀን ቆጥረው የመጡ ሰዎች ምግብና መጠጥ ይጋበዛሉ፤ ቡና ተፈልቶ ዱዓ ይደረግና ቡና ይጠጣል (ወ/ሮ አሚና ኢብራሂም፣ 13/2/2013፣ ጋቀ፣ ቃመ)፡፡

አራስ ከሰባተኛ ቀን እጥበቷ ጀምሮ በቀን አንድ ወይም ሁለት ጊዜ ቀለል ካለ ጭስ እንድትጀምር ተደርጐ ቅቤ እየተቀባች የወይባ ጭስ እንድትሞቅ ይደረጋል፡፡ የወይባ ጭስ ሰውነትን ያጠብቃል፣ ያጠነክራል፣ አራስ ነፋስ እንዳይገባት ይከላከላል፣ ከሞቁት በኋላ እንቅልፍ ያስወስዳል፣ እረፍት ይሰጣል፣ ከውበት አንፃርም ሆድን ይሰበስባል፣ ቆዳ ያሳምራል፣ ቆዳ እንዳይሸበሸብ ያደርጋል ተብሎ ስለሚታመንበት አራስ በተደጋጋሚ እንድትሞቅ ይደረጋል፡፡ ከወይባው በኋላ ገላዋን ታጥባ ታጥቦ የተሞቀ ልብስ በመልበስ ጥሩ መዓዛ እንዲኖራት አዝጋሮና ሽታ ትሞቃለች (ወ/ሮ አሚና ኢብራሂም፣ 13/2/2013፣ ጋቀ፣ ቃመ)፡፡

### ለ. አቂቃ

አቂቃ የህፃኑ አባት ልጅ ማግኘቱን የሚመሰክርበት ሀይማኖታዊ መሰረት ያለው የግዴታ ስነ ስርዓት (Ismaiel num. 5049) ሲሆን በአብዛኛው ልጅ ተወልዶ በሰባተኛው ቀን ይከወናል፡፡ የስነ ስርዓቱ ክዋኔ ዋና መገለጫ የእርድ ስነ ስርዓት የሚከወን መሆኑ ነው፡፡ ሀይማኖታዊ በሆነ ደንብ (Abu Dawud num. 2842) ህፃኑ ወንድ ከሆነ ሁለት ፍየል ወይም በግ፣ ሴት ከሆነች ደግሞ አንድ ፍየል ወይም በግ ይታረዳል፤ የሚታረደው ፍየል ሁለት ዓመት እድሜ የሆነው፣ በግ ከሆነ ደግሞ አንድ ዓመት የሆነው መሆን አለበት፡፡ ከዚህ በተጨማሪም የሚታረደው ፍየልም ሆነ በግ አካሉ ያልጐደለ መሆን አለበት፡፡ አቶ ኢብራሂም ይርጉ (22/5/2013፣ ገቀ፣ ቃመ) እንደገለፁት እርድ ከተከናወነ በኋላ ስጋው አጥንቱ ሳይሰበር ወይም ሳይከሰከስ መለያያ መለያያው ላይ ብቻ ተቆርጦ ይቀቀላል፡፡ ሲበላም ስጋው ከላዩ ላይ እየተላጠ ተበልቶ አጥንቱ አንድም ሳይቀር ተመልሶ ይሰበሰብና

በንፁህ ጨርቅ ተቋጥሮ ይቀበራል፡፡ የተጠሩ ደረሳዎችና[32] ሌሎች ወንዶች ምግብ ከበሉና ዱዓ አድርገው ቡና ከጠጡ በኋላ ሰለዋት ያደርጋሉ፡፡

### ሐ. ስም ማውጣት

በአርጎባዎች ዘንድ ስም በዋናነት በሶስት መንገድ ይወጣል፡፡ አንደኛው የህፃኑ ወላጆች የወላጆቻቸውን ወይም የሌላ ቤተሰባቸውን አባል ስም ለልጃቸው የሚሰጡበት፣ ሁለተኛው ቁርዓንን መነሻ በማድረግ ስም የሚወጣበት እና ሶስተኛው በአካባቢ የነበሩ በመንፈሳዊ ህይወታቸው የበቁ ሰዎችን መጠሪያ ለልጅ የሚሰጥበት መንገድ ነው፡፡ የህፃኑ ወላጆች ከእነዚህ ከስም ማውጫ አማራጮች መካከል የትኛውን መጠቀም እንዳለባቸው ተመካክረው ይወስናሉ (አቶ መሐመድ ዘይን ሲራጅ፣ 8/7/2013፣ አቀ፣ ቃመ)፡፡

### መ. ግርዛት

የተወለደው ህፃን ወንድ ከሆነ በሰባተኛው ቀን ወይም ከዚያ በኋላ ባሉ ቀናት ይገረዛል፡፡ ግርዛቱን የሚያከናውኑ የተለዩ ባለሙያዎች አሉ፡፡ ግርዛት ከተከናወነ በኋላ ቁስሉ ቶሎ እንዲደርቅ የኮሶ ቅጠል በጨርቅ ተቋጥሮ በቅቤ እየተሞቀ ቁስሉ ይተኮሳል (ወ/ሮ ፋጡማ መሐመድ፣ 9/7/2013፣ አቀ፣ ቃመ)፡፡

ይህ የሽግግር ጊዜ ወላዷ ከነፍሰጡርነት ጊዜዋ የምትነጠልበትና አዲስ ማንነትን ለማግኘት ግን ጊዜው ያልደረሰላት የምትሆንበት ጊዜ ነው፡፡ ይህ ጊዜ ወላዷ በምጥና በወሊድ ጭንቅ የምትያዝበትና መስዋዕትነት የምትከፍልበት፣ በነፍሰጡሯ አካባቢ ያሉ ሰዎችም የሚጨነቁበት፣ ነፍሰጡሯ ምጧ እንዲገራና በሰላም እንድትገላገል የምጥ አግሪዎቹ ስም እየተጠራ ልመና የሚደረግበት፣ ዱዓ የሚደረግበት ነው፡፡ ከወሊድ በኋላም ምንም እንኳን ይህን መሰሉ ጭንቀት የቀነሰ ቢሆንም ወላዷ አራስ በመሆኗ ለህመም የተጋለጠች ነች ተብሎ የሚታሰብ በመሆኑ በመኝታዋ አካባቢና ለሽንት በምትወጣ ጊዜ የህመም መከላከያ መያዟና ብቻዋን እንዳትሆን መደረጉ፣ እርሷና ህፃኑ በምግብና በንጽህና እንክብካቤ የሚደረግላቸው መሆኑ፣ አራሷ በፈሰሳትና በሚፈሳት ደም ምክንያት ንፁህ እንዳልሆነች ስለሚቆጠር ፆም የማትፆም፣ ስግደት የማትሰግድና ፆታዊ ግንኙነት የማታደርግ መሆኗ፣ የቤት ውስጥ ስራዎችን የማታከናውንና በማህበራዊ ህይወት ውስጥ የማትሳተፍ መሆኗ ይህ ነው በሚባል ደረጃ ላይ አለመሆኗን የሚገልፁ ሁኔታዎች ናቸው፡፡

### 5.3. መቀላቀል

ወላዷ በወለደች አርባኛ ቀን በምታደርገው እጥበት ቀደም ሲል ወደነበረው ህይወቷ፣ ወደ ቤተሰቧና ወደ ማህበረሰቡ የምትቀላቀል በመሆኑ የአርባኛ ቀን እጥበት ዋና የመቀላቀያ ስነ ስርዓት ነው፡፡ የአርባ ቀን እጥበት እንደሌላው ቀን እጥበት የንጽህና ጉዳይ ብቻ ሳይሆን ከዚያ ከፍ ያለ ትርጉም ያለው የመንፃትና የመሻገር እጥበት

[32] የህይማኖት ተማሪዎች

ነው፡፡ አራስ በወሊድ ጊዜና ከዚያ በኋላ በፈሰሳት ደም ምክንያት ንፁህ እንዳልሆነች የሚታሰብ በመሆኑ በወለደች አርባኛ ቀን የግዴታ እጥበቷን በመታጠብ ንፁህ ካለመሆን ንፁህ ወደመሆን ትሸጋገራለች (አቶ መሐመድ ሰዒድ ዳውድ፣ 8/7/2013፣ አቀ፣ ቃመ)፡፡

በአርባ ቀን እጥበት የሰባት ቀን እጥበት ጊዜ የነበረውን ዓይነት የተስፋፋ ስነ ስርዓትና ብዙ ሰው አይኖርም፡፡ የአራሷን እጥበት አስታውሰው የሚሄዱ በቁጥር ጥቂት የሆኑ ሴቶች ብቻ ሊኖሩ የሚችሉ ሲሆን የሚጋበዙትም ቤት ያፈራውን ነው (ወ/ሮ ጀሚላ አሕመድ፣13/7/2013፣ ጉቀ[33]፣ ቃመ)፡፡ በእለቱ ቡና ተፈልቶና ዳቦ ተቆርሶ ዱዓ ከተደረገና ቡናው ከተጠጣ በኋላ አራሷ ትታጠባለች፡፡ አራሷ ገላዋን ታጥባ ከጨረሰች በኋላ ከመውለዷ በፊት የተሰራውን ፀጉሯን ፈትታ እንደገና ትሰራለች፤ ቅቤ ተቀብታ አዝጋሮና ሽታ ትሞቃለች፡፡ አርባ ቀን የአራስነት ማብቂያ በመሆኑ አራሷ የተኛችበት አልጋ ወጥቶ በሰባተኛው ቀን በታጠበበት መንገድ ታጥቦ ለፀሀይ ይሰጣል፤ ልብሷም ይታጠባል (ወ/ሮ ከዲጃ መሐመድ፣ 13/7/2013፣ ጉቀ፣ ቃመ)፡፡

አራስ አርባ ቀን ሆኗት የግዴታ እጥበቷን እስከምትታጠብ ድረስ ንፁህ እንዳልሆነች ስለሚታሰብ ፆም አትፆምም፤ ስግደትም አትሰግድም፤ ከባለቤቷ ጋር ፆታዊ ግንኙነት አታደርግም (Abu Dawud num. 311)፡፡ የአራስነት ጊዜዋ ስላላለቀና ሰውነቷም ያልበረታ ስለሆነ የቤት ውስጥ ከባድ ስራዎችን አትሰራም፤ ወደ ውጭ ወጥታ በማህበራዊ ኑሮ እንቅስቃሴ ውስጥ አትሳተፍም፤ አራስ በመሆኗ መከላከያ የሚሆናት ብረት አይለያትም፡፡ ነገር ግን ከእጥበቱ በኋላ አራሷ የአራስነት ጊዜዋ ያበቃል፤ ፆም መፆምና ስግደት መስገድ፣ ፆታዊ ግንኙነት ማድረግ፣ አብዛኛዎቹን የቤት ስራዎችን መስራት፣ ቀስ በቀስ በማህበራዊ ኑሮ ውስጥ መሳተፍና የበሽታ መከላከያ ብረት መተው ወይም አለመያዝ ትጀምራለች (ወ/ሮ እሙ መነልከሪም፣ 14/7/2013፣ ጉቀ፣ ቃመ)፡፡ በዚህ መልኩ ቀደም ወዳለው ህይወቷ ትመለሳለች፤ ነገር ግን ስትመለስ ቀደም ሲል የነበራት ማንነት በተወሰነ መጠን ይቀየራል፤ የምትመለሰው በተለየ የእናትነት ገጽታ ይሆናል፡፡

እነዚህ የመዋቅር ደረጃዎች ከህፃኑ አንፃር ሲታዩ ህፃኑ የሚነጠለው በወሊድ ጊዜ እትብት ሲቆረጥ ነው፡፡ ህፃኑ ከሚያውቀው የቀደመ ዓለም፣ ከእናቱ ማህፀን ወጥቶ አዲስ ዓለምን የሚቀላቀልበትና ከእናቱ የሚለይበት ነው፡፡ የሽግግር ጊዜው ደግሞ ተወልዶ እትብቱ ከተቀረጠበት ጊዜ ጀምሮ እስከ ሰባተኛው ቀን እጥበት ዋዜማ ድረስ የሚቆይ ነው፡፡ በዚህ ጊዜ ውስጥ ህፃኑ አዲስ ወደሆነ ዓለም ይምጣ እንጂ ወደ ማህበረሰቡ ያልተቀላቀለበት ጊዜ ነው፡፡ በዚህ ጊዜ ህፃኑ በምግብ፣ በንጽህናና ጤንነቱን በተመለከተ እንክብካቤ እየተደረገለት ይቆያል፡፡ የህፃኑ የመቀላቀያ ጊዜ ከሰባተኛው ቀን እጥበት የሚጀምር ነው፡፡ የሰባተኛ ቀን እጥበት ቀን የህፃኑ አባት አቂቃ በማድረግ ልጅ ማግኘቱን በይፋ የሚያሳውቅበትና ለህፃኑም ስም የሚወጣበት

---

[33] ጉዜ ቀበሌ

ቀን በመሆኑ ህፃኑ ለማህበረሰቡ የሚተዋወቅበትና የሚቀላቀልበት ነው፡፡ አዲስ ህፃን ወደ ምድር መምጣቱን በመመስከርና መጠሪያ የሚሆነውን ስም በመሰየም ህፃኑ ለማህበረሰቡ ይተዋወቃል፡፡

## 6. ማጠቃለያ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ ከአርጎባ ብሔረሰብ የህይወት ሽግግር ስነ ስርዓቶች መካከል የወሊድ ስነ ስርዓትን ክዋኔ መተንተን ነው፡፡ በጥናቱ የአርጎባ ብሔረሰብ በወሊድ ጊዜ የሚከውናቸው ስነ ስርዓቶች ምን ምን ናቸው; የክዋኔው መዋቅር ምን መልክ አለው; በክዋኔው ውስጥ ያሉ ሌሎች የፎክሎር ዓይነቶች ምን ምን ናቸው; በስነ ስርዓቱ ውስጥ ያሉ ትዕምርቶች ምን ምን ናቸው; ስነ ስርዓቱ ለከዋኞቹ የሚሰጠው ግለሰባዊና ማህበራዊ ጠቀሜታ ምንድን ነው; የሚሉ ጥያቄዎች መልስ አግኝተዋል፡፡

በጥናቱ የአርጎባ ብሔረሰብ ባህላዊ የወሊድ ስነ ስርዓት ክዋኔ፣ መዋቅር ትዕምርትና ፋይዳ ቀርቧል፡፡ የብሔረሰቡ የወሊድ ስነ ስርዓት ክዋኔ መዋቅሩ ከ Gennep የሶስት ደረጃ ሞዴል (መለየት፣ ሽግግርና መቀላቀል) አንፃር ለሶስት ሊከፈል የሚችል ነው፡፡ ይህም አንዲት ሴት ነፍሰጡር መሆኗ ከታወቀ በኋላ ከነበረችበት ማህበረሰብና ከቤተሰቧ አባላት ትለያለች፡፡ በዚህ ጊዜ የሚከወኑ ለነፍሰጡሯ የሚደረግ እንክብካቤ፣ የሚጣሉባት ክልክሎችና የሚሰጣት ምክር ነፍሰጡሯን ከፆታ አቻዎቿና ከማህበረሰቡም ተለይታ እንድትታይ የሚያደርጉ ናቸው፡፡

የሽግግር ጊዜ ነፍሰጡሯ የመውለጃ ጊዜዋ ደርሶ ምጥ ከጀመራት ጊዜ ይጀምርና ነፍሰጡሯ ወልዳና የአራስነት ጊዜዋ እስከሚያበቃበት አርባኛ ቀን ዋዜማ ድረስ ያለውን ጊዜ ይይዛል፡፡ ይህ ጊዜ ከወሊድ በፊት ነፍሰጡሯ አዲስ ማንነትን ለማግኘት ጊዜው ያልደረሰላት፣ በምጥና በጭንቅ የምትያዝበት፣ በዙሪያዋ ያሉ ሰዎች የሚጨነቁበትና ዱዓ የሚደረግበት ጊዜ ነው፡፡ ከወሊድ በኋላም በአራስነቷ ምክንያት ለህመም የተጋለጠች ተደርጋ የምትታሰብበት በመሆኑ አራሷንና ልጇን ከህመም ለመጠበቅ የተለየ እንክብካቤ የሚደረግላቸው፣ አራሷም ለህመም መከላከያ እንዲሆናት በራስጌዋ ብረት የምታስቀምጥበት፣ ለሽንት ስትወጣም እንዲሁ ብረት የምትይዝበትና በፀጉሯ ላይም የምታደርግበት፣ በወሊድ ምክንያት ንፁህ እንዳልሆነች የሚታሰብ በመሆኑ ቀደም ሲል ታከናውናቸው የነበሩ ተግባራትን የማታከናውንበት ጊዜ መሆኑ አራሷ በሽግግር ውስጥ ያለች መሆኗን የሚያሳይ ነው፡፡

የመቀላቀል ደረጃ ከአርባኛው የእጥበት ቀን የሚጀምር ሲሆን ከዚያ በኋላ አራሷ ቀደም ሲል ወደተነጠለችው ማህበረሰብ፣ የፆታ አቻዎቿና የቤተሰቧ አባላት በተለየ ማንነት ትቀላቀላለች፤ ያለህመም መከላከያ መንቀሳቀስ ትጀምራለች፤ በአራስነት ጊዜዋ ንፁህ እንዳልሆነች በመታሰቡ ምክንያት እንዳታደርግ ትከለከላቸው የነበሩ ተግባራትንም ማከናወን ትጀምራለች፡፡

በጥናቱ በብሔረሰቡ የወሊድ ስነ ስርዓት ክዋኔ ውስጥ ያሉ ቃላዊ፣ ቁሳዊና ድርጊታዊ ትዕምርቶች ተለይተው ፍቺዎቻቸውም የቀረቡ ሲሆን ክዋኔው ማህበራዊ፣ ስነ ልቡናዊ፣ እሴቶችን የመትከልና ጤና የማስገኘት ፋይዳ ያለው መሆኑ በጥናቱ ተለይቷል፡፡

በጥናቱ በብሔረሰቡ የወሊድ ስነ ስርዓት ክዋኔ ውስጥ ያሉ የፎክሎር አይነቶች የተለዩ ሲሆን እነርሱም ስነቃል (ዱዓዎች፣ ዝኪሮች፣ መማፀኛዎች፣ መልካም ምኞትን መግለጫዎች፣ ምሳሌያዊ አነጋገሮች፣ ዝየራዎች)፤ ቁሳዊ ባህል (ባህላዊ ምግብና መጠጥ (ትዕምርታዊ የሆኑትንም ጨምሮ)፣ ሽታ፣ አልባሳት፣ የማዋለጃ ቁሳቁሶች፣ የእንግዴ ልጅ መቅበሪያ ቁስ፣ ገላ መታጠቢያ ቅጠላ ቅጠል) እና ማህበራዊ ልማድ (እምነቶች፣ ባህላዊ ሕክምና (መንፈሳዊና የእጽዋት ሕክምና)፣ ስም አወጣጥ፣ የፀጉር አሰራር፣ ጭስ መሞቅ) ናቸው፡፡ የጥናቱን ግኝቶች መሰረት በማድረግ የሚከተሉት የይሁንታ ሀሳቦች ቀርበዋል፡፡

- ዘመናዊ የህክምና ተቋማት ባህላዊውን የወሊድ ስነ ስርዓት ክዋኔ ግብዓት በማድረግ የነፍሰጡር ማረፊያዎቻቸውንና ማዋለጃዎቻቸውን ሁኔታ በብሔረሰቡ ባህል መሰረት ማስተካከል ቢችሉ ግባቸውን ማሳካት ይችላሉ፤ የባህላዊውን ስነ ስርዓት ቀጣይነትንም ማረጋገጥ ይቻላል፡፡ ለምሳሌ በጋቸኔ ቀበሌ ጤና ጣቢያ ውስጥ ለወላዶች ማረፊያ ተብሎ የተሰራው ባህላዊ ጐጆ ለታሰበለት ዓላማ እንዲውል የማመቻቸት ስራ ቢሰራ፣
- ነፍሰጡር ያሉባት የምግብ ክልክሎች ነፍሰጡሯ ከምግብ ልታገኝ ከሚገባው ንጥረ ነገር አንፃር የሚያሳጣት ነገር መኖር አለመሆኑ በወረዳው የጤና ጽ/ቤት ጥናት ተደርጐ ቢለይ፣
- በወሊድ ጊዜ የሚከወኑ አንዳንድ ክዋኔዎች ለምሳሌ፣ መነቅነቅ፣ ሆድ ማሸትና የመሳሰሉት ከጤና አንፃር ወላድ ላይ የሚያስከትሏቸው የጤና ጉዳቶች ካሉ ይኸው ሁኔታ በወረዳው የጤና ጽ/ቤት ጥናት ተከናውኖ ጉዳቱ ቢለይ፡፡

**የተጠቀሱ ምንጮች**

ለማ ንጋቱ፡፡ 2006፡፡ "የለቅሶ ሥርዓት ክወና በደቡብ ጎንደር ዞን"፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ በፎክሎር የዶክትሬት ዲግሪ ማሟያ ጥናት (ያልታተመ)፡፡

ስራዬ እንዳለው፡፡ 2005፡፡ "የህይወት ዘመን ዑደት ሽግግር ደረጃዎች ስርዓተ ክዋኔ በፍኖተ ሰላም አካባቢ ከፎክሎር ከዋኔ ንድፈ ሀሳብ አንፃር"፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ለኢትዮፕያ ስነጽሁፍና ፎክሎር መርሀ ግብር የኤም.ኤ ዲግሪ ለማግኘት ከሚያስፈልጉ ነጥቦች ከፊሉን ለማሟላት የቀረበ ጥናት (ያልታተመ)፡፡

ነጋሽ መሐመድ፡፡ 1981፡፡ "አርጐብኛና የአርጐቦች ህይወት በሁለት /አልዩ አምባና አዋሽ/ ከተሞች ውስጥ"፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡፡ በኢትዮፕያ ቋንቋዎችና

ስነ ጽሁፍ ክፍል ለአርትስ ባችለር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት (ያልታተመ)፡፡

አህመድ መህመድ ኢብራሂም፡፡ 1999፡፡ *በኢትዮጲያ የማክዙማይትና የሃሺማይት ወላስማ ስርወ-መንግስት ስልጣኔና ታሪክ የአርጐባ ሕዝብ የመነሻና የማንነት ግንዛቤ*፡፡

አበባ አማረ፣ ደስታ አማረ እና ፍሬህይወት ባዩ፡፡ 2015፡፡ "የሕይወት ኡደት ባህላዊ ክዋኔና ሥርዓት በስልጤ"፡፡ In *Some Features of Diversity of Ethiopian Languages and Cultures*. Vol. 2, 2-115. Addis Ababa University, Addis Ababa University business enterprise printing press.

አዲሱ ጴጥሮስ፡፡ 2000፡፡ "የአርጐባ ማህበረሰብ የማንነት ቃላዊ ዝርው ተረኮች ትንተና"፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ በኢትዮጰያ ስነጽሁፍና ፎክሎር የኤም.ኤ ዲግሪ ለማግኘት ከፊሉን ለማሟላት የቀረበ ጥናት፡፡ (ያልታተመ)፡፡

አፀደ ተፈራ፡፡ 2007፡፡ "የዋግኽምራ የወሊድ የጋብቻ እና የሞት ሥነ-ሥርዓት ፋይዳ ትንተና"፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ በፎክሎር መርሃ ግብር የዶክትሬት ዲግሪ ማሟያ ጥናት፡፡ (ያልታተመ)፡፡

እታገኘሁ አስረስ፡፡ 2010፡፡ "የአርጐባ ብሔረሰብ አፋዊ ትውፊቶችና መገለጫዎች ጥበቃ ጥናት"፡፡ *የአራተኛው አገር አቀፍ የባህል አውደ ጥናት መድበል*፡፡ ደብረ ብርሃን ዩኒቨርሲቲ፡፡ 143-173፡፡

ዐቢዩ አስማማው፡፡ (2005)፡፡ "የአርጎባ ብሄረሰብ የቤት ውስጥ መገልገያና የማጌጫ ቁሶች፣ በአማራ ክልል ደቡብ ወሎ ዞን፣ አርጎባ ልዩ ወረዳ"፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ለኢትዮጲያ ስነጽሁፍና ፎክሎር መርሀ ግብር ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት፡፡ (ያልታተመ)፡፡

ደስታ አማረ፡፡ 2007፡፡ "የህይወት ኡደት (የወሊድ፣ የጋብቻና የሞት) ስርዓቶች ክዋኔ ትንተና በወሊሶ ሊበን ኦሮሞ"፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ በፎክሎር መርሃ ግብር የዶክትሬት ዲግሪ ማሟያ ጥናት፡፡ (ያልታተመ)፡፡

ድርብወርቅ ብፁ፡፡ 2007፡፡ "የጉምዝ ብሔረሰብ ዋና ዋና የሕይወት ዘመን ኡደት ሽግግር ደረጃዎች ሥርዓት በማንዱራ ወረዳ"፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ በአማርኛ ቋንቋ ሥነጽሁፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት የኤም.ኤ ዲግሪ ለማግኘት ከፊሉን ለማሟላት የቀረበ ጥናት፡፡ (ያልታተመ)፡፡

Abebe Kifleyesus. 1992. "The dynamics of Ethnicity in a plural polity: Transformation of Argobba social identity". Northwestern University. A Dissertation submitted to the Graduate School in partial fulfillment of the requirements for the degree of doctor of philosophy in the field of Anthropology. (unpublished).

Abu Dawud, I. H. 2008. *Sunan Abu Dawud*. Trans. Al-Khattab, Nasiruddin. Vol. 3. Darussalam.

___________. 2008. *Sunan Abu Dawud*. Trans. Qadhi, Yaser. Vol. 1. Darussalam.

Aklilu Asfaw. 2000. "A Short History of the Argobba". *Annals d'Éthiopie*. XVI, 173-183.

Barnard, A. and Jonathan Spencer. 1996. "Rite of passage". *Encyclopedia of Social and Cultural Anthropology*. London, Routledge, 737-738.

Bell. C. 1997. *RITUAL Perspectives and Dimensions*. Oxford: Oxford University Press.

Bronner, S. J. (ed.). 2007. *The Meaning of Folklore the Analytical Essays of Alan Dundes*. Utah, Utah State University press.

Feinberg B. 2004. "Passage, Rites of". *Encyclopedia of Religious Rites, Rituals, and Festivals*. New York. Routledge, 311-314.

Gennep, A. V. 1960. *The Rites of Passage*. Chicago: University of Chicago Press.

Grimes, R. L. 2000. *Deeply into the Bone Re-inventing rites of Passage*. London, University of California Press.

Han, J. H. 2004. "Birth Rituals". *Encyclopedia of Religious Rites, Rituals, and Festivals*. New York. Routledge, 48-52.

Ismaiel, M.I. 1997. *Sahîh Al- Bukhâri*. Trans. Khan, Muhammad Muhsin. Vol. 6. Darussalam.

Longhurst, R. 1999. “Pregnant Bodies, Public Scrutiny ‘Giving’ advice to pregnant women.” In *EMBODIED GEOGRAPHIES Spaces, bodies and rites of passage*, edited by Elizabeth Kenworthy Teather. 77-88. London. Routledge.

Malinowski, B. *A Scientific theory of Culture and other Essays*. The University of North Carolina Press.

Mazama, A. 2009. "Rites of Passage" *Encyclopedia of African Religion*. California, SAGE Publications, Inc., 570-574.

Pentikäinen, J. "Ritual". 2011. *FOLKLORE: An Encyclopedia of Beliefs, Customs, Tales, Music, and Art*. Santa Barbara, ABC-CLIO, LLC, 1104-1110.

Radcleffe-Brown, A. R. 1952. *Structure and Function in Primitive Society*. Glencoe. The Free Press.

Seid Muhie. 2015. "Documentation and Description of the Rekebot Traditional Conflict Resolution System of the Argoba Community". Addis Ababa University. Presented in partial fulfillment for the requirements for the degree of Master of Arts in Documentary linguistics and Culture. (Unpublished).

Seligman, A. B. et al. 2008. *Ritual and Its consequences An Essay on the limits of sincerity*. Oxford, Oxford University Press.

Shujaa, M. J. 2009. "Rituals". *Encyclopedia of African Religion*. California, SAGE Publications, Inc., 575-579.

Sims, M. C. and Martine Stephens. 2005. *Living Folklore An Introduction to the Study of People and Their Traditions.* Utah. Utah State University Press.

Storey, J. 2018. *Cultural Theory and Popular Culture An Introduction*. London. Pearson Longman.

Tesfaye Hailu. 2000. "History and Culture of the Argobba". *Annales d'Ethiopie*. XVI, 195-206.

*The Quran*. 2005. Translated by M.A.S. Abdel Haleem, Oxford university press.

Trimingham, J. S. 1965. *Islam in Ethiopia*. FRANK CASS and CO. LTD..

Turner, V. 1982. *From Ritual to Theatre The Human Seriousness of Play*. New York. PAJ Publications.

Waldron, S. R. 1984. "Argobba". *Muslim Peoples: A World Ethnographic Survey*. In Richard V. Weekes (Ed.). Greenwood Press. 49-54.

Watts, J. W. 2007. *Ritual and Rhetoric in LEVITICUS from sacrifice to scripture*. Cambridge, Cambridge University Press.

Kaufman, S. R and Lynn M. Morgan. 2005. "The anthropology of the Beginnings and ends of Life". *The Annual Review of Anthropology*. 34, 317-341.